የደኅንነትና የእድገት ትምህርት

ፓ/ር አስፋው
በቀለ

የጽዮን ክብር ቤተ ክርስቲያን

ለአዲስ አማኝ ክርስቲያኖች በግልም ሆነ ከአስተማሪ ጋር ለመማር የሚረዳ መማሪያ

ይህች ትንሽ መጽሐፍ መዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣
መንፈሳዊ እደገት እንዴት እንደምናገኝና ቤተ ክርስቲያንን፣
ቅዱስ ስርዓቶችንና አገልግሎትን ምን ማለት
እንደሆነ ታስተምራለች።

ማውጫ ገጽ

ምዕራፍ አንድ - ደህንነት	**4**
ሀ. የእግዚአብሔር እቅድ	6
ለ. የሰው ውድቀት	5
ሐ. የሰው ሙከራ	8
መ. የእግዚአብሔር መፍትሄ	9
ሠ. የእግዚአብሔር መፍትሄ	11
ረ. የሰው ድርሻ	14
ምዕራፍ ሁለት - ዕድገት	**19**
ሀ. የደኅንነት ማረጋገጫ ማግኘት	19
ለ. በክርስቶስ ማደግ	21
• የጥሞና ጊዜ	23
• ጸሎት	24
• ቃሉን ማንበብ	27
• ኅብረት	31
• ክርስቶስን መታዘዝ/መቀደስ	33
• መመስከር	35
• በመንፈስ ቅዱስ መሞላት	39
ሐ. ደቀ መዝሙር	41
ምዕራፍ ሦስት - ቤተ ክርስቲያን	**44**
ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድናት?	44
ለ. ቤተ ክርስቲያን የምትመሰልባቸው ምሳሌዎች	46
ሐ. ሁሉን አቀፍና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን	50
መ. የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶች	54
1. የውኀ ጥምቀት	54
2. የጌታ ራት	58
ምዕራፍ አራት - አገልግሎት	**61**
ሀ. የአገልግሎት ምንነት	61
ለ. በማገልገል ማደግ	64

1. ድነት (መዳን)

ሀ፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ (የንባብ ክፍል፡ ዘፍ.1-2)

ማንም ሰው ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው የእርሱንም መንግስት ለመውረስና ከእርሱም ጋረ ለዘላለም ለመኖር ይመኛል። እግዚአብሔር አምላክ በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥረውም በዕቅድና በዓላማ ነበር። ዓላማውንም እግዚአብሔር አስቀድሞ የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ እንዲገዛና ከእግዚአብሔርም ጋር ኅብረት ኖሮት ለዘላለም እንዲኖር ነበር።

የሰው አፈጣጣር ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ነበር። ሌሎቹ በቃል ሲፈጠሩ ሰው ግን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ፣ ከአምላክ ጋር ህብረት ለማድረግ እንዲችል መንፈስ ያለው መሆኑ፣ የሚያስብና የሚያስተውል አዕምሮ ያለው መሆኑ፣ ክፉውን ከመልካሙ በመለየት በወደደው መንገድ ለመሄድ የሚያስችል ፈቃድና ህሊና ያለው መሆኑን ያጠቃልላል።

አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ በእነዚህ መልካም ነገሮች ብቻ የተሞሉ አልነበሩም። በውጪና በዙሪያቸው ከሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ምንም ያልጎደላቸው ነበሩ። አየር ህልውና አብሯቸው ነበር። እግዚአብሔር አብሯቸው ከኖረ ኑሯቸው ሙሉ ነው ማለት ነው። ዕረፍት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ የዘላለምም ህይወት አላቸው። ይህን ህብረት እስከጠበቁ ድረስ ደግሞ ክፉ ነገር አያገኛቸውም ሞትንም አይሞቱም።

ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅድ ምን ነበር?

2. የሰውን አፈጣጠር ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

3. ሰው በአምሳለ አምላክ ተፈጠረ ሲባል ምን ማለት ነው?

4. ሰው ከአምላክ ጋር ህብረት ሲኖረው ውጤቱ ምንድን ነው?

ለ፡የሰው ውድቀት

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ስጦታ አንዱ የምርጫ ነጻነት ሲሆን ይህን ያደረገው ሰው ያለግዴታ በፈቃደኝነት እንዲታዘዘውና እንዲከተለው ሲል ነው። ይህን ፈቃደኝነቱን ለማረጋገጥም በዔደን የአትክልት ስፍራ እንዳይበሉ የተከለከሉት ዛፍ ነበር (ዘፍ.2፡9)። አዳምና ሔዋን ፈቃድ ቢኖራቸውም ኃጢአትን ላለመስራት ችሎታም ነበራቸው። እግዚአብሔር መታዘዛችን ከፈቃዳችን እንዲመነጭ ይሻል። እርሱ የሚወደው በምርጫችን ስንገዛለት ነው።

ሰይጣን በተንኮሉ ሔዋንን በማሳት ሰውን ሁሉ በደለኛና ዓመጸኛ አደረገው። አዳም እንዳይበላ የታዘዘውን ዛፍ ፍሬ በመብላት ሰይጣንን መታዘዝን ወይም እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ መረጠ። ባለመታዘዙም ኃጢአትን ሰራ፤ አስቀድሞም የተመደበውን ፍርድ ተቀበለ። ፍርዱም ሞት ነበር። (ዘፍ.2፡16-17) ይህ ሞት ስጋዊ ሞት ሳይሆን መንፈሳዊ ሞት ሳይሆን መንፈሳዊ ሞት ነበር። ይህም ከአምላክ መለየት ነበር፤ ይሁን እንጂ ስጋዊ ሞትም የዚህ ፍርድ አንድ ቅርንጫፍ ነው። የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ የሆነው አዳም በኃጢአት በመውደቁ ሰው ሁሉ በኃጢአት አዘቅት ውስጥ ወደቀ። (ሮሜ.5፡12)

ኃጢአት ሰውን ከአምላኩ፣ ከሌላ ሰው ፣ከራሱ እንዲሁም ከተፈጥሮም ጋር ሳይቀር አጣላ። በተለይም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የጥልን ግድግዳ አኖረ። የሰውንም ዘር ሁሉ ከማህጸንም ጀምሮ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየ እንዲሆን አደረገ። (መዝ.51፡5) አዳምን ሔዋን የሰያንን አሳብ ከሰሙና ከታዘዙ፤ በኃጢአትም ከወደቁ በኋላ ከእግዚአብሔር ፊት ተደበቁ።

ድምጹን ሲሰሙ ይደነግጡ ፊቱንም ሊያዩ ይፈሩ ጀመር። ስለዚህም ከፊቱ በርግገው በጫካ መደበቅን መረጡ። ይህ ነገር በእነርሱ ብቻ ሳያበቃ ዛሬም ሰው ሁሉ በደለኛ በመሆን ከኃጢአት በታች ወድቆ፣ ከእግዚአብሔርሔር ክብር ጎድሎ፣ ፍርደኛ በመሆን ከአምላኩ እየሸሸ እንዲኖር አድርጎታል። (ሮሜ.3፡23) በአንዱም በአዳም ኃጢአት ሁላችን ኃጢአተኞች ሆንን ሁላችንም ሞትን።፡(1ቆሮ.15፡22)

ዛሬ የምናያቸውና የምንሰማቸው እጅግ የበዙ መጥፎ ድርጊቶችና ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ኃጢአት ናቸው። ከዚህ በላይ ግን እነዚህ ነገሮች የዋናው ኃጢአት ማለትም እግዚአብሔርን የመሸሽ ቅርንጫፍና ውጤቶች ናቸው። እውነተኛ መፍትሔ ለማግኘት መደረግ ያለበት ቅርንጫፎችን መመልመል ሳይሆን ስርን መንቀል ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ሰው ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝ የተዘጋጀው መፈተኛ ምን ነበር? ለምንስ ተዘጋጀ?

2. አዳምና ሔዋን ላለመታዘዝ ይችሉ ነበር? ያለመታዘዛቸውስ ፍርድ ምን ነበር? ውጤቱስ?

3. የአዳምና የሔዋን መተላለፍ በሰው ዘር ላይ ያመጣው መዘዝ ምንድን ነው?

ሐ፡ የሰው ሙከራ



ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣላና ከተለያየ በኋላ ከእርሱ ጋር ለመታረቅ እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ መንገድ ሞክሯል። ሰው ሲፈጠር ከአምላኩ ጋር ኅብረት በማድረግ ሳይለያይ ለመኖር ነበርና የተፈጠረው ይህ እስካልሆነ ድረስ ነፍሱ ዕረፍትን አታገኝም። በእርሱና በአምላኩ መካከል የተፈጠረውን የኃጢአት ገደል ሞልቶ ሊያሻግረው የሚችል ድልድይ ከማበጀት ታክቶ አያውቅም።

ህግን በመጠበቅና ለማድረግ በመታገል ተሞክሯል፣ ጨዋና በጎ አድራጊ በመሆን እግዚአብሔር ሊደረስ ተሞክሯል፣ የተለያዩ ኃይማኖቶችን በመከተል ሊደረስ ተሞክራል፣ የተለያዩ ትምህርቶችንና ፍልስፍናዎችን በመከተል ለመታረቅ ተሞክሯል፣ ራስን በመጉዳት የኃጢአትን ዋጋ በመክፈል ለመታረቅ ተሞክሯል፣ ሌሎችም ተደርገዋል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ሰው ሰራሽ ድልድዮች ወደ እግዚአብሔር ማድረስ የሚችል ባህርይም አቅምም ያላቸው አይደሉም።

ጥያቄዎች፡

1. ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው ዕረፍት የሌለው ለምንድነው?

2. ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እስከዛሬ ድረስ ምን ምን መንገዶች ሞክረዋል?

መ፡ የእግዚአብሔር መፍትሔ

1. በብሉይ ኪዳን

ሰው በኃጢአቱ ይውደቅ እንጂ እግዚአብሔር ግን ጥሎ አልተወዉም። ከውድቀቱ ሊያነሳውና ከኃጢአቱም ሊያነጻው መድኃኒት እንዳዘጋጀለት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን። አዳምና ሔዋን ከተላለፉና ከተሸሸጉ በኋላ እግዚአብሔር ወደተሸሸጉበት መጣ። እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅ አምላክ ነውና ፍርዱንም መፈጸም ነበረበትና እርምጃው ወዲያውኑ ተወሰደ። አሳቹ ተረገመ፣ አዳምና ሔዋን ከአምላክ ተለይተው ከኤደን ገነት ተባረሩ፤ እንዳይገቡም ተደረጉ።እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ብቻ ሲችል ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ግን የተስፋ ቃልን ሰጣቸው። (ዘፍ.3፡15) ሌላው ያደረገላቸው ነገር ዘላቂ ልብስን ማልበሱ ነው። አዳምና ሔዋን ዕርቃናቸውን በቅጠል ሊሸፍኑ ሞከሩ። ይህ በራስ እጅ የራስን ኃጢአት መሸፈን እንደማይቻል ያሳያል። እነርሱን የቁርበት ልብስ ለማልበስ አስቀድሞ የታረደ እንስሳ መኖሩንና ደም መፍሰሱን ያመለክታል።

ኃጢአት የነፍስ ዋጋ መጠየቅ የጀመረው ከአዳምና ከሔዋን ጊዜ ሲሆን መታረቅም የደም ዋጋ መጠየቅ የጀመረው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚህ ጊዘ አንስቶ የመጨረሻውና ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ጾም መስዋዕት ለማቅረብ ተገደዱ። ደም ሳይፈስ ስርየት ሊገኝ አልተቻለም። ከዚህ ጊዜም ብዙ ቆይቶ የተሰጠው የሙሴ ሕግ ለኃጢአት ስርየት የነፍስን መስዋዕትና የደምን መፍሰስ ጠይቋል። (ዘፍ.4፡4፤ 8፡20፤ ዘሌ.17፡11፤ ዕብ.9፡22)

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርና ሰዎች ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ የተሰጣቸው የሙሴ ህግ ነበር። ይህን ካፈረሱ የደም መስዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው። በዚህም የኃጢአትን ጊዜያዊ ስርየት ያገኙ ነበር። ይህ የመታረቂያ መንገድ እግዚአብሔር ለጊዜው ያዘጋጀው እንጂ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ የተሰራው ዘላቂው መንገድ አልነበረም።

ጥያቄዎች፡

1. ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ምን ሆነ? እግዚአብሔርስ ምን አደረገ?

2. በብሉይ ኪዳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁበት የነበረው መንገድ ምን ነበር?

3. ለኃጢአት ስርየት ደም መፍሰስ ማስፈለጉ የኃጢአትን ክብደት ምን ያህል ያመለክታል?

መ፡ የእግዚአብሔር መፍትሔ (የንባብ ክፍል 1ዮሐ.5፥6-21)

2. በአዲስ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን የተገለጠው የደኅንነት መንገድ በአዲስ ኪዳን ወደተገለጠው ዘላቂው መንገድ እንደሚያመራ ያለ መጋቢ መንገድ ነው። ሕግ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ነው። (ገላ.4፥24) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የአዳኝ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ይህም አዳኝ ከሴት የተወለደው ደግሞም ከሕግ በታች የተወለደው፣ ሥጋ የለበሰው አምላክ፣ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ገላ.4፥4-5)

በስጋ የተገለጠው ይህ ኢየሱስ ንጹህ ደሙን በማፍሰስ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደው የእግዚአብሔር በግ ነው። ይህን ተስፋ ነበር እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የሰጠውና በአዲስ ኪዳን የገለጠው። ኢየሱስ ክርስቶስ የደኅንነት ብቸኛና እውነተኛ መንገድ ነው (ዮሐ.14፥6)። በብዙ ኃይማኖቶች እንደምናየው ሰዎች በራሳቸው ጥረትና መፍጨርጨር እግዚአብሔርን ሊያገኙ ሲሞክሩ ነው። ሰዎች በራሳቸው ጥረትና መፍጨርጨር እግዚአብሔርን ሊያገኙ ሲሞክሩ ነው። ለምሳሌ በሚከተሉት መንገድ፦

- ሰውነታቸውን በመጉዳት
- ዓለምን ክዶ በመመነንና በብትህና በመኖር
- በጎ ስራን ተግቶ በመስራት
- የተወሰኑ ሕግጋትንና ድንጋጌዎችን በመጠበቅ
- የአንድ የእምነት ድርጅት አባል በመሆንና በመሳተፍ

ሌሎችንም ብዙ ብዙ ነገሮችን በማድረግ አንድ ቀን ሲሞቱ የእግዚአብሔር መንግስት ወራሾች ለመሆን ይለፋሉ። ኃጢአተኛ ሰው በጥረቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣ ከእርሱም ጋር ኅብረትን መፍጠርና መንግስቱንም መውረስ አይችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ግን ኃጢአት ወደ ሰው ታሪክ ከገባ በኋላ ሰው ከፈጣሪው የሚሸሽና እግዚአብሔር ደግሞ ከነአዳምም ጀምሮ ኃጢአተኞችን ፍለጋ የሚመጣ አምላክ መሆኑን

ነው። ማንም ሰው በኃጢአተኛው ተፈጥሮ እግዚአብሔርን የማይፈልግ መሆኑን በሮሜ.3፡11 ላይ ተጽፏል። በሉቃስ 19፡10 ጌታ የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን እንደመጣ ተናግሮአል።

በአዲስ ኪዳን የተገለጠው የደኅንነት መንገድ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ፈልጎን ነው የመጣው። አምላክ ሳለ ሰው በመሆን፣ ፈተናዎችን ሁሉ በማለፍ ያለኃጢአት በመሆን፣ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመሞት፣ ሞትንም ድል አድርጎ በመነሳት ለሚያምኑት የዘላለም ህይወት ምንጭና ወደ አብ የሚያደርሰው ብቸኛ ድልድይ ሆኗል።

ከሴቲቱም የሚወለደው ዘር የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥ የተሰጠው ተስፋ ቃል ከድንግል ማርያም በተወለደው በክርስቶስ ተፈጸመ። እንግዲህ ደኅንነት ወይም የዘላለም ህይወት በስራችንና በጥረታችን የምናገኘው የስራችን ፍሬ ሳይሆን እንደ ስጦታ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ከምንባቡ ክፍል በተለይም ከቁጥር 12 እንደምናገኘው የሕይወት ምንጭ ማነው? ጥቅሱን በራስህ አገላለጽ ጻፈው።

2. ሰዎች ለመዳን ከሚያደርጓቸው ነገሮች ጥቂቶቹን ዘርዝር። አንተስ ምን ታደርግ ነበር?

3. እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ ምንድን ነው?

4. እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠው ተስፋ የተፈጸመው እንዴት ነው?

5. ክርስቶስ ስጋ የለበሰበት ዓላማ ምንድን ነው?

ሠ. የሠው ድርሻ (የንባብ ክፍል ዮሐ.3)

ሰው ከኃጢአት ሊድንና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረው የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ መሆኑን ተመልክተናል። ይህ ማለት ከኃጢአት ንስሃ በመግባት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳዔ አምኖ ጌታን በመቀበልና ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም አዲስ ፍጥረት መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ቢያዘጋጅም ሰው ግን ካልተቀበለው ሊድን አይችልም።

ደኅንነትን በተመለከተ የሰው ድርሻ መቀበል ብቻ ነው። ዮሐ.1፡12 ጌታን ለተቀበሉትና በስሙ ለሚያምኑት እግዚአብሔር ልጆቹ የሚሆኑበትን ስልጣን እንደሰጣቸው ይናገራል። ጌታን መቀበል ማለት እርሱን አውቆ አዳኝና ጌታ አድርጎ በግል ፈቃድ መወሰን ማለት ነው። ይህ ውሳኔ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ነው። ጌታን ማወቅና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የደኅንነት መንገድ መረዳት ደኅንነት አስፈላጊ ነገር ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ያልበሰለ አ ዕምሮ ያለው ሕጻን ጌታን ሊቀበልና ደኅንነትን ሊለማመድ አይችልም። (ዕብ.11፡6)

ደኅንነት በእምነት የምንቀበለው ስጦታ ነው። እምነት የተስፋ ማረጋገጫና የማይታይ ነገር ማስረጃ ነው። (ዕብ.11፡1) ደህንነት በአ ዕምሮአችን አውቀን የምንጨርሰው ነገር አይደለም። ያልገቡንና ተረድተን ያልጨረስናቸው ወደፊት ሙሉ በሙሉ የማንፈጽማቸው ነገሮች ይኖራሉ። ቢሆንም እምነት ማለት ባወቅነው የእግዚአብሔር ቃል መታመንና ያንንም መኖር ማለት ነው። የምናምነው እምነት ለአዕምሮአችን ለመቀበል ይከብደው ይሆናል። የ እግዚአብሔር ቃል ግን እውነት ነውና፤ ሁሉ ነገራችንን ለዚያ እውነት ማስገዛት ይገባናል።

ይህ የባቡል ስዕል በደኅንነት ውስጥ የቃሉን፣ የእምነትንና የስሜቶችን ቦታና ሚና ያሳያል። የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም ቀዳሚ መሆን አለበት። እምነታችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፍ አለበት። ስሜቶቻችን ሁሉ ደግሞ ለእምነታችን መገዛት አለባቸው።



ባቡሩን በከሰል ኃይል እንደሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ብንወስደው የመጀመሪያው ክፍል የሞተሩን ቤት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የከሰል ክፍል ሲሆን ሦስተኛው የመዝናኛ ፉርጎ ነው። የሞተሩ ቤት እስካለ ድረስ ባቡሩ መሄድ ይችላል። እንዲንቀሳቀስ ግን ከከሰሉ ፉርጎ ከሰሉን ማለትም እምነታችንን በሞተሩ ፉርጎ ማለትም በእግዚአብሔር ቃል ማድረግ ያስፈልገናል። ከሰሉን በተገቢው ቦታ ማለትም በቃሉ ላይ እንጂ ያለቦታው ማለትም በስሜታችን ላይ ማድረግ የለብንም። በተመሳሳይ ሁኔታ የፈለገው ያህል እምነት በስሜታችን ላይ ብናደርግ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የትም አያደርሰውም።

አንዳንድ ሰዎች ማመን ስሜታዊነት ብቻ ይመስላቸዋል። ሌሎች ደግሞ በእምነት ውስት ስሜት ከቶ እንደሌለ ይቆጥራሉ። ሁለቱም ስህተት ነው። የስሜት ህልውና የማንክደው ነገር ነው። ክርስትና ስሜታዊነት ባይሆንም ስሜት የለሽነት ደግሞ አይደለም። ይሁን እንጂ ለማመን ወይም በእምነት ለማደግ በስሜቶች መደገፍ ትክክል አይደለም።

መዳን ማለት ከዘላለማዊ ሞት ወደ ዘላለማዊ ህይወት፣ ከሲኦል ፍርድና ከኩነኔ ወደ ምህረትና ጽድቅ፣ ከእግዚአብሔር ጠላትነት ወደ ወዳጅነት፣ ለሰይጣን ከመገዛት የእግዚአብሔር ልጅ ወደመሆን ማለት ነው። ኢየሱስን በግል እንደ አዳኝና እንደጌታ አድርጎ በመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ማለት ነው። “የግል” ሲባል ክርስቶስ የኔን የራሴን ኃጢአትና በደል ተሸክሞ ሞቶልኛል ማለት ነው። ኃጢአት ስንል ሁለት ዓይነት እንደሆነ ማየቱ ተገቢ ነው። “አዳኝ” ሲባል እንግዲህ ከ እነዚህ የሚያድነን መሆኑንና በኃጢአታችን ምክንያት መሞት ሲገባን በፈንታችን ሞቶ ያዳነን ወይም ደኅንነትን የሰጠን መሆኑን የሚያሳይ ነው። ኢየሱስ የሚለው ስም ትርጉም ራሱ አዳኝ ወይም መድኃኒት ማለት ነው። “ጌታ” ስንልም አንድ ክርስቲያን ጌታን

ከተቀበለ ጀምሮ ሕይወቱንና ኑሮውን የሚመራውና የሚቆጣጠረው ራሱ ሳይሆን በውስጡ ማደር በጀመረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጌታ ኢየሱስ የህይወቱ ጌታ መሆኑን ሲያሳይ ነው።





እነዚህ ሁለት ስዕሎች ራሱን የሚቆጣጠር ሰውና ጌታ የሚቆጣጠረው ሰው ምን እንደሚመስሉ ያሳየናል። መስቀሉ የክርስቶስን ህልውና ሲያሳይ በመጀመሪይው ስዕል ውስጥ በዙፋኑ ላይ ያለው ራሱ (እ=እኔነት) ሲሆን በመስቀሉ የተመሰለው ክርስቶስ ከሰውየው ውጪ ነው። ህይወቱም ግራ የተጋባ ነው። n

በሁለተኛው ስዕል እንደሚታየው ግን የሰውየው እኔነት የንጉስነት ቦታውን ለክርስቶስ መልቀቁንና በዙፋኑ ላይ ላለው ዝቅ ብሎ እየተገዛ መሆኑን ያሳያል። ጌታን መቀበል ማለት ክርስቶስን በሚገባው ቦታ ማለትም በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በህይወታችን፣ በኑሮአችን፣ በትዳራችንና በሌሎችም በማናቸውም መስኮች ላይ ጌታ እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው?

2. ኢየሱስን የግል አዳኝና ጌታ በማድረግ መቀበል ምን ማለት ነው?

3. ኢየሱስን ጌታው ያደረገና ያላደረገ ሰው ልዩነታቸው ምንድን ነው?

4. እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ደኅንነት ለማግኘት ሰው ማድረግ ያለበት ምንድን ነው?

5. ደኅንነትን ለመቀበል ማወቅ ያስፈልጋል ስንል ምን ማለታችን ነው? መታወቅስ ያለበት ነገር ምንድን ነው?

6. ደህንነትን የምንቀበለው በእምነት ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

7. ለደኅንነት ውሳኔ የፈቃድ አስፈላጊነት ምን ያህል ነው?

8. ደህንነትን ወይም እምነትን በስሜት ላይ ማስደገፍ የማይገባን ለምንድነው?

2. ዕድገት

ሀ. ደኅንነትን ማረጋገጥ (መዳናችንን ማረጋገጥ)

እግዚአብሔር መዳናችንንና የዘላለም ህይወት ማግኘታችንን ያለምንም ጥርጣሬ እንድናውቅ ይፈልጋል። ይህን ነገር እርግጠኛ ያልሆነ አማኝ በመንፈሳዊ ህይወቱ ማደግም ሆነ የጌታው ታማኝ ምስክር ሊሆን ይሳነዋል። እነዚህን ጥቅሶች ያንብቧቸው፦ (ዮሐ.3፡16-18፤5፡24፣ 6፡37፤ ሮሜ.8፡1-3፣ 8፡31-39፣10፡13፤ ኤፌ.1፡13-14፤1ዮሃ.4፡15-17፤5፡13።)

የደኅንነት እርግጠኝነትን ማለት በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ተለይቶና ርቆ ሲኖሩ ቆይቶ በክርስቶስ የመስቀል ላይ መስዋዕታዊ ሞት ድኖ የዘላለም ህይወትን ማግኘትን ማመንና እርግጠኛ ሆኖ ማወቅ ነው። አንድ አማኝ ደኅንነትን ሲያገኝ ወይም ዳግም ሲወለድ የሚሰማው ስሜት ሊኖር ወይም ላይኖር ይችላል። ስሜት ጥሩ ነገር ቢሆንም ነጂ መሆን እንደሌለበት ከባቡሩ ስእል ተመልክተናል።

አንድ አማኝ ዳግም በተወለደባት ቅጽበት የሆነውና የተፈጸመው እጅግ ድንቅ ነገር ነው። አንድ አዲስ አማኝ ማወቅ ካለበት ነገሮች መካከል በቃሉ መሠረት ክርስቶስ ወደ ህይወቱ እንደገባ፣ የቀደመው በደልና ኃጢአት ሁሉ ይቅር እንደተባለ፤ ከዘላለም ሞትና ፍርድ እንደዳነ፣ ከጨለማው ስልጣንና ከሰይጣን ግዛት እንደተላቀቀና ነጻ እንደወጣ፣ ካመነበት ወይም ራሱን ለጌታ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የጌታ ማደሪያ እንደሆነ፣ አዲስ ፍጥረት እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር ልጅና ቤተሰብ እንደሆነ፤ ዳግም እንደተወለደ፤ በአለም ላይ ካሉት ስጦታዎች ሁሉ እጅግ የላቀና ተወዳዳሪ የሌለውን የዘላለም ህይወት እንዳገኘ ናቸው።

ያ አዲስ ክርስቲያን በዳነ ጊዜ አዲስን ልዩ ግንኙነት በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ተፈጥሯል። አንድ አዲስ ክርስቲያን ደኅንነቱን እርግጠኛ ሲሆን በዚያች ቅጽበት ቢሞት እንኳ ወዴት እንደሚሄድ በእርግጠኝነት ይሞላል።

ጥያቄዎች፡

1. እግዚአብሔር መዳናችንን እንድናውቅና እርግጠኛ ልንሆን እንደሚወድ በምን እናውቃለን?

____

____

____

____

2. ደኅንነትን እንዳገኙ እርግጠኛ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

____

____

____

____

3. ስለ ደኅንነት እርግጠኝነት ማረጋገጫ መፈለግ ያለብን ከየት ነው?

____

____

____

____

4. ስለ ደኅንነት ምን ያህል እርግጠኛ እንደሆንክ ከታች ባለው መስመር የ “x” አድርግ።

0% ____________________ 100%

ለ. በክርስቶስ ማደግ

መወለድ ማለትም ዳግም መወለድ የመንፈሳዊ ህይወት ጅማሬ ነው። ከአካላዊ ልደት በኋላ አካላዊ ዕድገት እንደሚጀምር ከመንፈሳዊ ልደት በኋላ መንፈሳዊ ዕድገት ይጀምራል። በመንፈስ ያላደጉ ክርስቲያኖች ህፃናት ይባላሉ (1ቆሮ.3፡1፣ 1ጴጥ.2፡2)። ከዚያም ልጆች፣ ጎበዞች (ወይም ወጣቶች) እየተባሉ ይጠራሉ (1ዮሃ.2፡12-14)። መንፈሳዊ ዕድገት በክርስትና ህይወት መጎልመስና መብሰል ነው (1ዮሃ.2፡12-14) ።

መንፈሳዊ ዕድገት በክርስትና ህይወት መጎልመስና መብሰል ነው። በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ አማኞች ለማደግ የተለያዩ ነገሮች እንደሚያስፈልጋቸው ግልጽ ነው (1ቆሮ.3፡1-3፤ ዕብ.5፡ 12-14)።

ህፃናት ምግብ የሚሹ፣ ድጋፍና ዕርዳታ የሚፈልጉ፣ በቀላሉ የሚታለሉ፣ ክፉን ከደጉ ለይተው የማያውቁ ብቻቸውን ሲሆኑ ምስኪ የሆኑ ነገሮች ናቸው። አዲስ የተወለዱ መንፈሳዊ ህጻናትም ተመሳሳይ ናቸው። ትንሽ ማደግ ሲጀምሩ እንክብካቤው እየቀነሰ ራሳቸው የራሳቸው ረዳቶች እየሆኑና ለራሳቸው ጎልውና እየተጠነቀቁ መታዘዝ እየጀመሩና የአቅማቸውን እያበረከቱ፣ እያስተዋሉና እየበሰሉ ይሄዳሉ። ይሁን እንጂ ብዙ ይቀራቸዋል።

በመንፈሳዊ ህይወትም ለጋ የሆኑ እንዲሁ በመጠኑ ያወቁ ቢሆኑም ብዙ የሚቀራቸው ናቸው። በአካላዊ ዕድገት ወጣትነት፣ ጎልምስናና በሳልነት እንዳለ ሁሉ በመንፈሳዊ ህይወትም እንዲሁ ነው። መብሰል የክርስቲያን ዕድገት ግብ ነው። መንፈሳዊ ብስለት ከአካላዊ ዕድገት የሚለይበትም መንገድ አለ፤ ያም የክርስትና ዕድገት “በስያለሁ” ተብሎ የሚያቆሙት አይደለም።

አንድ ክርስቲያን ጌታን ከተቀበለና ዳግም ከተወለደ በኋላ በክርስቶስ ማደግ ይጠበቅበታል። በ2ጴጥ.3፡18 “በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ” ተብሎ ተጽፏል። ያለማደግ ያሳዝናል። በክርስትና ህይወት ያላደጉት ተወቅሰዋል። (ዕብ.5፡12-14) የማያድግ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገባውንና የሚጠበቅበትን ካለማበርከቱም ባሻገር በራሱም ላይ ችግር ፈጣሪ ሊሆን ይችላል።

በሃሰተኛ ትምህርቶችም በቀላሉ ሊወሰድ ይችላል። ስለዚህ አንድ አማኝ ጌታን ከተቀበለበት ቅጽበት አንስቶ ለማደግ መፈሳዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። የአንዳንዶች የዕድገት ፍጥነት ከሌሎች ሊለይ ይችላል፤ ይሁን እንጂ ዕድገት የአጭር ጊዜ ሳይሆን የህይወት ዘመን ሁሉ ልምምድ ነው። ህፃን ሲወለድ የሃያ ዓመት ወጣት ሆኖ እንደማይወለድ ክርስቲያንም ብስል ሆኖ አይወለድም። መወለዱ የሚያስገርም ልደት ቢሆንም፤ የገባው ወደሚያስደንቅ ቤተሰብ ቢሆንም፤ የሚወርሳቸውን ነገሮች እያወቀ የሚመጣው እያደር ነው። እየቆየም ይሁን እየፈጠነ፤ ማደግ ግን ይጠበቅበታል።

ጥያቄዎች፡

1. አካላዊ ዕድገትና መንፈሳዊ ዕድገት የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ____________________

____

____

____

2. መንፈሳዊ ብስለት ከአካላዊ ዕድገት የሚለይበት ባህርይስ ምንድን ነው? ______________

____

____

____

____

3. ማደግ ለምን አስፈለገ? የማያድግ ክርስቲያን ምን ችግር ይገጥመዋል? ______________

____

____

____

____

1. የጥሞና ጊዜ

የጥሞና ጊዜ ማለት አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው ልዩ የአንድነት ጊዜ ነው። ይህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ንባብና የጸሎት ጠምሮ የያዘ ጊዜ ነው። ሁለቱም አብረው የሚደረጉበትና የተወሰነ ጊዜና ቦታ ተሰጥቶት መቋረጥ ሳይኖርበት መደረግ ያለበት ነገር ነው። ቃሉ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ጸሎቱ ደግሞ ለእግዚአብሔር መናገር ነው። በአጭሩ የጥሞና ጊዜ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜና ቦታ ቀጥረን ያንንም አክብረን ተገናኝተን የምንነጋገርበት የግል ጊዜያችን ነው።

በማር.1፡35 እንደምንመለከተው ጌታ በማለዳ ገና ሌሊት ሳላ ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ እንደጸለይ ተጽፎልናል። ለክርስቲያንም እያንዳንዱ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በማድረግ የሚጀመር መሆን ይገባዋል። ይህ ኅብረት ክርስቲያን ለየቀኑ የሚሆነውን መንፈሳዊ ምግብ የሚቀለብበት የከበረ መለኮታዊ ገበታ ነው።

የጥሞና ጊዜ ከቃሉ እንደምንረዳው የጸጥታ ጊዜ ነው። ይህን ማለትም አማኙ ምንም ሌላ አሳብን የሚረብሽና የአሳብን አትኩሮት የሚሰርቅ ነገር በሌለበት ማንንም ሳይጨምር ለብቻው ከፈጣሪው ጋር የሚሆንበት ጊዜ ነው። በተቻለ መጠን ጊዜውም ሆነ ቦታው ባይለዋወጥ አሳብን ለማሰባሰብ ይበልጥ ይረዳል። ጊዜው የግድ ጠዋት መሆን ላይኖርበት ይችላል። አማኙ ጊዜን መምረጡ የአማኙ ፈንታ ነው። ጠዋት ወይንም ማለዳ መሆኑ ግን በብዙ አንጻር ጥቅም አለው። ብሩኅና የነቃ አዕምሮ እንዲሁም የታደሰና የበረታ አካል የሚኖረን በዚያ ጊዜ ስለሆነ ለጌታ ይህን ጊዜ ብንሰጠው በረከት አለው (ኢሳ.50፡4)።

የጥሞና ጊዜ በትንሹ ቢጀመርና እየጣመ ሲመጣ እያደገ ቢሄድ ይሻላል። በየቀኑ ለ10 ደቂቃ ሳያቋርጡ ማድረግ አንድ ቀን አንድ ሰዓት ሙሉ ቆይቶ ሌላ ጊዜ ለቀናት ካለማድረግ ይሻላል። የጥሞና ጊዜውን ሁለት ቦታ መክፈልና ከፊሉን ለቃል ንባብ፤ ከፊሉን ደግሞ ለጸሎት ማድረጉ

ተገቢ ነው። ከሁለቱ አንዳቸው ሊቀድሙ

<u>ጸሎት</u>

ጸሎት በቀላል ቋንቋ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና መነጋገር ማለት ነው። በሁለት ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት የሚያድገው በመነጋገር እንደመሆኑ መጠን የክርስቲያንና የእግዚአብሐርም ግንኙነት የሚዋበው በመነጋገር ማለትም በጸሎት ነው። ስንጸልይ ስለማናቸውም ነገር (ለምሳሌ:- ስለምሪት፣ ስለጥበቃ፣ ሰለሚያስፈልጉን ቁሳዊና አካላዊ ነገሮች፣ ስለሌሎች ጓደኞቻችን ደኅንነት ወዘተ.) በየትም ቦታ (ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በቤታችን፣ በምድረ በዳ ወዘተ.) በማናቸውም ጊዜ (ለምሳሌ:- በማለዳ፣ ጠዋት፣ ቀን፣ ማታ፣ ሌሊት) መጸለይ እንችላለን። ጸሎት በአንድ ክርስቲያን ህይወት ውስጥ የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና ሰይጣን ስለሚያውቅ ይህ እንዳይሆን የሞትና የሽረት ትግል ያካሂዳል።

ጸሎት የጌታ ትዕዛዝ እንጂ አማራጭ አይደለም (ማቴ.7፡7-11)። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግን ስለሚወድድ የጸሎትን መንገድ ከፍቶልናል። ጸሎት ለአንድ ክርስቲያን ልክ እንደ እስትንፋስ ያህል አስፈላጊ ነገር ነው። የማይጸልይ ክርስቲያን ልክ እንደማይተነፍስ ሰው ነው ማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል። መልሱ እሺ፤ ወይንም እምቢ፤ ወይንም ጠብቅ (ቆይ) ሊሆን ይችላል። ከኛ ልመና የተሻለ መልስ ስላለው እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ምሳሌዎችን ብንመለከት:-

- እሺ - 1ሳሙ.1- ለሃና፤ 2ነገ.20 - ለህዝቅያስ፤ 2ነገ.6 - ለኤልሳዕ፤ ሉቃ.17 - ለምጻሞቹ
- ጠብቅ - ዘፍ.15 - ለአብርሃም
- እንቢ - 2ሳሙ.12 - ዳዊት፤ ማቴ.26 - ጌታ ኢየሱስ፤ 1ቆሮ.12 - ጳውሎስ

በጸሎት ውስጥ አምስት ነገሮች ይካተታሉ:- እነዚህም ውዳሴ፣ ምስጋና፣ ንስሃ፣ ልመናና ምልጃ ናቸው።

- ውዳሴ - አምላክን እንደ አምላክነቱና በአጠቃላይ ስለሮሱነቱ ማምለክና ከፍ ከፍ ማድረግ ነው።
- ምስጋና - እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገሮች እያሰብን የምናመሰግንበት ጊዜ ነው።
- ንስሃ - ስለተላለፍናቸው ጥፋቶችና ኃጢአቶች ሁሉ የምንናዘዝበት ጊዜ ነው።

- ልመና - የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሄር ለአምላካችን የምንነግርበት ጊዜ ነው።
- ምልጃ - ስለሌሎቹ የምንጸልይበት ወይም የምንማልድበት ጊዜ ነው

በምንጸልይበት ጊዜ የተወሰነ የሰውነት አቋም የግድ ሊኖረን አያስፈልግም፤ መቆም፣ መቀመጥ፣መንበርከክ፣ በግንባራችን መደፋት፣ ቀና ወይም ጎንበስ ማለት፣ አይንን መዝጋት ወይም መክፈት እንችላለን። ብዙ ጊዜ ጎንበስ የሚባለውና አይን የሚጨፈነው ለአክብሮትና አሳብን ለመሰብሰብ እንጂ ግዴታ አይደለም። በማናቸውም ሁኔታ እንቅረብ ግን ከማን ጋር እየተነጋገርን መሆናችንን በማወቅ በትህትና እንቅረብ (ዘፍ.18፡22-23፤ ዘጸ.34፡8፤ ኢያሱ 7፡6፤ 1ሳሙ.1፡26፤ ማቴ.26፡39)።

ለመጸለይ የሚያስፈልገን ሌላ ነገር እምነት ነው። ያለእምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም (ዕብ.11፡6)። ስንጸልይ ግልጽ የሆነና ሲመለስልን መመለሱ የሚታወቅ ጥያቄ እናቅርብ። የጸሎታችንን መልስ ለማግኘት ደግሞ መታገስና መጽናት ያስፈልጋል (ሉቃ.18፡1-8)።

ከሰዎች ጋር ስንጸልይና ድምጻችን ለሌሎች የሚሰማ ከሆነ የሌሎችን አትኩረት ለመሳብ እንዳንሞክር መጠንቀቅ አለብን። ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገራችንን ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም (ማቴ.6፡6)። ስንጸልይ ደግሞ ሌላ ነገሮች እያሰብን የተለመዱና የተሸመደዱ ቃላት ብቻ አንደጋግም (ማቴ.6፡7)። ስንጸልይ መናገር ብቻ ሳይሆን ማድመጥም እንቻል፤ መነጋገር ማለት መናገር አይደለምና። እግዚአብሔር በዚህ ዘመን የሚናገረንና የሚያሳስበን ዋና መንገድ ቅዱስ ቃሉ፤ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የጸሎት መመሪያችንም መሆን ያለበት ህያው ቃሉ ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ጸሎት ማለት ምን ማለት ነው?

2. ጸሎት መቼ፣የትና ስለምን መደረግ አለበት?

3. እግዚአብሔርን ጸሎታችንን ሊመልስ የሚችልባቸው ሦስት መንገዶች ምን ምን ናቸው?

4. በጸሎት ውስጥ የሚካተቱት አምስት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

5. እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚወደው ለምንድነው?

6. ጸሎት ለታይታ መሆን የሌለበት ለምንድነው?

ቃሉን ማንበብ



አንድ ክርስቲያን ማድረግ ያለበት ሌላ ዋና ነገር መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ነው። አዲስ የተወለደ ህጻን ወይም ግልገል ጡት መጥባት በደመ ነፈስ እንደሚጓጓ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በአጭር ቋንቋ እግዚአብሔር ራሱንና የማዳን ዕቅዱን በሰዎች ታሪክ ውስጥ የገለጠበት እውነት የተዘገበበት መጽሐፍ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና አዲስ ኪዳን በመባል ሁለት ቦታ ይከፈላል፤ አሮጌው ቃል ኪዳንና አዲሱ ቃል ኪዳን እንደማለት ነው። ቃል ኪዳን የሚለውን ቃል ስምምነት ልንነው እንችላለን። ይህ ቃል ኪዳን ወይም ስምምነት እግዚአብሔር ሰዎች እንዲድኑ ያዘጋጀውን መንገድ ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን የነበረው በመቶ የሚቆጠሩ ትዕዛዛትን በመጠበቅና ከተሳሳቱም ለመታረቅ የእንስሳ ደም የሚያፈስ ሱበት ስርዓት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከተሰቀለና ከተሰዋ በኋላ ግን አዲስ ስርዓት ማለት አዲስ ኪዳን ተጀመረ። ከዚያ በኋላ ደኅንነት ሕግጋትን በመጠበቅና መስዋዕትን በማቅረብ መሆኑ ቀርቶ በክርስቶስ ስራ በማመንና እርሱን በመቀበል ሆነ።

በጠቅላላው በመጽሐፍ ቅዱስ 66 መጽሃፍት ሲኖሩ፤ 39ኙ በብሉይ ኪዳን 27ቱ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። በሙሉ ተጽፈው ለመፈጸም ከ1500 አመታት በላይ የፈጀ ሲሆን የጻፏቸውም ከ40 የማያንሱ የተለያዩ ሰዎች ናቸው። ቃሉ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ በተመሩ ሰዎች ነው (2ጴጥ.1፡21)፤ ደግሞ ቃሉ ራሱ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት ነው (2ጢሞ.3፡16)፤ ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ያለው።

የብሉይ ኪዳን መጽሃፍት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነዚህም ዖሪት፣ታሪክ፣ቅኔያትና ነቢያት ናቸው። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትም እንዲሁ አራት ቦታዎች ይከፈላሉ። እነዚህም ወንጌላት፣ታሪክ መልዕክተኞችና ትንቢት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ምንነቱን ማወቅ ብቻ ሳይሆን አንድ ክርስቲያን ምን ማድረግ እንዳለበት የሚከተለው ስዕል ይነግረናል፡-

- *ትንሿ ጣት* - መስማትን ትወክላለች። ሮሜ.10፡17 እንደሚነገረን መስማት ትልቅ ነገር ነው። ከዚያ በላይ ማድረግ የሚቻል ከሆነ ደግሞ መደረግ አለበት። በትንሿ ጣት ብቻ መጽሐፍ ይዞ ማቆየት እንደማይቻል ሁሉ በመስማት ብቻ ቃሉን መያዝ አንችልም።

- *የቀለበት ጣት* - ማንበብን ይወክላል። ራዕ.1፡3 እንደሚያስተምረን ማንበብ ብጽዕና አለው። ማንበብ የሚችል ክርስቲያን ሁሉ የጌታን ቃል ማንበብ ኃላፊነት አለበት።

- *የመሃል ጣት* - ማጥናትን ያመለክታል። በሐዋር.17፡11 እንደተጻፈልን የቤርያ ክርስቲያኖች ቃሉን ዕለት ዕለት ያጠኑ እንደነበር እናያለን። ማጥናት ማለት በግልም ይሁን በቡድን ግን በስርዓት ቃሉን መብላት ማለት ነው።

- *አመልካች ጣት* - በቃል መሸምደድን ይወክላል። መዝ.119፡11 ቃሉን በልብ ውስጥ የመሰወርን ጠቃሚነት ይናገራል። ቃሉ የሰይጣንን ፈተና የምንቃወምበትም ነውና በልባችን መያዙ ለውጊያው ይበልጥ ይረዳናል።

- *አውራ ጣት* - ማሰላሰልን ያመለክታል። ማሰላሰል ማለት ደግሞ ደጋግሞ ደጋግሞ ማሰብ ማለት ነው። እንስሳት የበሉትን እንደሚያመነዥጉት እንደማለት ነው። በመዝ.1፡2-3 ላይ የ እግዚአብሔርን ቃል በቀንና በሌሊት የሚያስበው ሰው የለመለመ ህይወት

እንደሚኖረው ተጽፏል። ቃሉን በአንድ ጣት መያዝ እንደማንችል ጣቶቹ ሲጨመሩ ደግሞ ይበልጥ በጥንካሬ እንደምንይዝ ግልጽ ነው።

- *መዳፍ* - የመታዘዝ አመልካች ነው። ቃሉን ብንሰማና ብናነብ፣ ብናጠናና ብንሸመድድ፣ ስናሰላስለውም ውለን ብናድር የማንታዘዘውና የማናደርገው ከሆነ ራሳችንን እያታለልን መሆናችንን ቃሉ ራሱ ይነግረናል (ያዕ.1፡22)። መጽሐፋችንን በጣቶቻችን ብቻ ከመያዝ በመዳፋችንም ስንይዘው አጥብቀን ልንይዘው እንደሚቻለን እንዲሁ ቃሉንም ስንታዘዘው ብቻ ወደ ውስጣችን ዘልቆ ይገባል።

አንድ ክርስቲያን እንግዲህ በማያወላዳ ሁናቴ ከቃሉ ጋር በቂ ጊዜ ማጥፋት ይገባዋል። ከስህተት ትምህርቶችና አሰራሮች ለመጠበቅ ቃሉ የግድ መታወቅ አለበት።

ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው? ____________________

2. መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጽሃፍት ስንትና ምን አይነት ናቸው? ____________________

3. አንድ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ የሚገባው ለምንድነው? ____________________

4. አንድ ክርስቲያን ቃሉን በሚገባ ለመረዳት መውሰድ ያለበት ስድስት ርምጃዎች ምን ምን ናቸው? ____________________

5. የእግዚአብሔርን ቃል ይበልጥ ለማወቅ አንተስ/ቺስ ምን እያደረግህ/ሽ ነው?

4. ኅብረት (የምንባብ ክፍል መዝ.(133))

እያንዳንዱ አማኝ ለማበረታታትና ለጥበቃ በአማኞች ኅብረት ውስጥ መሆን ተገቢው ነው። የክርስትናን ህይወትና የጌታን ቃል ይበልጥ በተግባር ማየት የሚችለው በአማኞች ኅብረት ውስጥ በመሆን ነው። ልክ አንድ ብላቴና እያየ እንደሚማር ማለት ነው። ኅብረት ማለት ክርስቲያኖች አንድነት ነው።

ኅብረት የሚገለጽበት ዋና መስክ ቤተ ክርስቲያን ናት። አንድ ሰው ጌታ በመቀበል ደኅንነትን ሲያገኝ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን የአንድ ትልቅ ቤተሰብ ክፍል ሆኗል። እንዲሁም ያ ሰው የአንድ አካል ብልት ሆኗል (1ቆሮ.12፡12-27) በአካል ውስጥም እንዳለ ብልት ጥቅም፣ተግባርና ኃላፊነት አለው። ቁርጭምጭሚት ወይም ክርን፣ ጣፊያ ወይም የሃሞት ከረጢት፣ ጆሮ ወይም አይን ሊሆን ይችላል እንደማለት ነው። ሁሉም አስፈላጊና ተደጋጋፊ ናቸው። አንድም የማያስፈልግን ብልት የለም።

ኅብረት ብዙ ጥቅሞች አሉት፡- ምሳሌ፡-

1. የክርስቲያኖች መታወቂያ የሆነው ፍቅር የሚገለጠው በኅብረት ውስጥ ነው (ዮሃ.13፡34-35)
2. በኅብረት ውስጥ መሞራረድና መሳሳል አለ (ምሳሌ.27፡17)
3. ጥንካሬ፣ ሙቀትና ጥበቃ አለ (መክ.4፡9-12)
4. የጌታ መገኘት አለ (ማቴ.18፡20)
5. ለአለም ጥሩ ምስክር መሆን ይቻላል (ዮሃ.17፡21)
6. የአካል ብልቶች ነንና እርስ በርስ እንፈላለጋለን፤ ማለትም ለየብቻ በመሆን ምንም መስራት አንችልም (1ቆሮ.12፡12-27)

በኅብረት ውስጥ ወይም ክርስቲያኖች በኅብረት በሚሆኑበት ጊዜ ምን ያደርጋሉ? የአማኞች ኅብረት በተግባር የሚገለጥ ነው። በአንድነት በሚሆኑበትም ጊዜ ቃሉን ማጥናትና መጸለይ (ሐዋ.2፡42) አንዱ የሌላውን ጥቅም መፈለግ (1ቆሮ.10፡24)፣ አንዱ የሌላውን ሸክም መሸከም

(ገላ.6፡2)፣ ማምለክ፣ እውነትን በፍቅር መነጋገርና እርስ በርስ መገነባባት (ኤፌ.4፡15-20)፣ እርስ በርስ ለመጠነካከር መገሳሰጽና መመካከር (ዕብ.3፡13)፣ አንዱ ሌላውን ማገልገል (1ጴጥ.5፡5-6) ይገኙባቸዋል።

ጥያቄዎች

1. ኅብረት ማለት ምን ማለት ነው? ለአዲስ አማኞችስ ምን ይጠቅማል?____________________

   ____

   ____

   ____

2. ከኅብረት ጥቅሞች ጥቂቶቹን ዘርዝር____

   ____

   ____

   ____

   ____

3. በኅብረት ውስጥ ከሚካተቱ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን ዘርዝር__________________________

   ____

   ____

   ____

4. አንተስ/ቺስ በክርስቲያኖች ኅብረት ውስጥ እንዴት እየተሳተፍክ እንደሆነ ጻፍ______________

   ____

   ____

   ____

5. ክርስቶስን መታዘዝ/መቀደስ

አንድ ሰው ክርስቲያን ሆነ ማለት ጌታን ጌታው አደረገ ማለት ነው። በልቡ ዙፋን ላይ የነገሰው ጌታ ክርስቶስ ነው። ሰው ለሚገዛለት ለዚያ ነገር ባሪያ ነው፤ እኛም ሰውነታችንን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ አድርገን ልናቀርብ ይገባናል (ሮሜ.6፡15-23)።

አንድ ጌታ ያለው ሰው ወይም እንበል አንድ ባሪያ የራሱ ሳይሆን የጌታውን አሳብ ብቻ እንደሚፈጽም፤ ክርስቶስ ጌታው የሆነ ሰውም የ እግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ነው መፈጸም የሚገባው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምን እናውቃለን እንል ይሆናል፤ የጌታ ፈቃድ በቅዱስ ቃሉ የተጻፈልን ነው። የእርሱስን ፈቃድ ማወቅ ለማወቅ እንግዲህ ቃሉን ማወቅ ያሻል ማለት ነው።

ያለመታዘዝ ብዙ ጠንቅና መዘዝ አለው። ለምሳሌ፡- በኢያሱ 7 የአካንን ታሪክ በ1ኛ ሳሙኤል 15 የሳዖልን ታሪክ፣ በመሳፍንት 14-16 የሳምሶንን ታሪክ ብናይ ባለመታዘዝ ያገኛቸውን ክፉ ነገር እናያለን። የታዘዙና የተባረኩም በብዛት እንዳሉ ከቃሉ እንረዳለን። አብርሃም እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነው (ዕብ.11፡8)። ክርስቲያን የተጠራው ጌታን ሊታዘዝ ነው (ፍል.2፡12)።

መታዘዝ ማለት በአጭር ቃል ክርስቲያን እንደመሆናችን መጠን ማድረግ የማይገቡንን ነገሮች ሁሉ ያለማድረግና ማድረግ የሚገቡንን ነገሮች ሁሉ ደግሞ ማድረግ ነው። ይህ ድርጊታችንን ንግግራችንንና አልፎም አስተሳሰባችንን የሚጠቀልል ነው። መታዘዝ ማለት በሌላ አገላለጽ በቅድስና መኖር ማለት ነው። ቅድስና ማለት ደግሞ መለየት ማለት ነው። ይህም መለየት ስጋን፣ ነፍስን፣አዕምሮንና ስሜቶችን ሁሉ ከሚያቆሽሹ ነገሮች ፈቅዶ መለየትና መራቅ ማለት ነው። መቀደስ ክርስቶስን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ነው (1ጢሞ.4፡8)።

በዚህች ምድርና በዚህ ስጋ ውስጥ ስለምንኖር ለርኩሰት ተጋልጠናል፤ ሰይጣንም ሁሌ መረቡ ውስጥ ተመልሰን እንድንገባለት ይፈልጋል። ይህ እንዳይሆን ልንተጋ ያስፈልገናል። ተግባራዊ በሆነ መንገድ መታዘዝ ወይም መቀደስ ማለት ለምሳሌ ወደ ክፉ ከሚመሩ መጥፎ አመል ካላቸው ጓደኞች መለየትን፣ ወደ ኃጢአት ከሚጋብዙ ቦታዎች መራቅን ወደ መጥፎ ተግባር ከሚመሩ

የሚነበቡና የሚታዩ ነገሮች መታቀብንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በአንጻሩ ደግሞ ከመጥፎ ነገር በሸሸን ልክ መልካም የሆነውን መከታተል እንደሚገባን መዘንጋት የለበትም። (1ጢሞ.6፡11-12)።

ጥያቄዎች፡-

1. ክርስቲያን ከባሪያ ጋር የሚመሳሰልበት መንገድ እንዴት ነው?____________________

2. የመታዘዝና ያለመታዘዝ ምሳሌዎች ሊሆኑን የሚችሉ ሰዎች እነማን ናቸው?____________

3. መታዘዝ ወይም መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ምንንስ ያጠቃልላል?______________

4. ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለመቀደስ መደረግ ካለባቸው ሁለቱን ጥቀስ።_______________

6. መመስከር



መመስከር ማለት በጥሬው ሲተረጎም ያዩትን የሆነውን የደረሰውን መናገር ማለት ነው። አንድ ሰው ለምስክርነት ሲቆም የሚምለው "እውነትን ብቻና እውነትን በሙሉ እናገራለሁ" ብሎ ነው። በክርስትና አተረጓጎም ደግሞ መመስከር ማለት ወንጌልን ማብሰር ማለት ነው። ወንጌል (evangellion) የግሪክ ቃል ሲሆን በአማርኛ ትርጓሜው የምስራች ማለት ነው።

ወንጌልን የምስራች ያደረገው ዋና ነገር በመጀመሪያው ትምህርት (ማለትም በምዕራፍ አንድ) እንደተረዳነው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ከተለያየ በኋላ ነው። በአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው ይህ የምስራች በጌታችን በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት ኃጢአተኞች መዳንንና የዘላለም ህይወትን ማግኘታቸው ነው። አንድ ክርስቲያን ሲመሰክር ማጋነንም ሆነ ከእውነቱ መቀነስ አይገባውም። መመስከር ደግሞ ለመርታት መከራከር ማለት አይደለም።

አንድ ክርስቲያን ጌታ ያደረገለትን ነገር ለሌሎች ሲናገር በተለይም የጌታን አዳኝነትና በጌታ ያገኘውን ይህን ደኅንነት ለሌላ ላልዳነ ሰው ሲናገር ያ መመስከር ይባላል። ጴጥሮስና ዮሃንስ ተዝቶባቸው በኢየሱስ ስም ከቶ እንዳይናገሩ ሲነገራቸው የተናገሩት እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም።" ብለው ነበር (ሐዋ.4፡20)። ለምንድነው? መመስከር ያስፈለገው? ጥቂት ዋና ዋና ምክንያቶችን እንመልከት፡-

1. ሰዎች ክርስቶስን ሊያውቁ የሚችሉበት ምስክርነት ብቻ ነው። ሰዎች የሚድኑት በጌታ በማመን ብቻ ከሆነ ይህን ጌታ ማወቅ አለባቸው (ሮሜ.10፡13-14)
2. የዳንን ሌሎችም ድነው እኛ ያገኘነውን በረከት እንዲያገኙ እንመኛለን፤ በዮሃ.4፡35-52 ሁለት ሰዎች ለሌሎች ሁለት ሰዎች እንዴት እንደመሰከሩ እናገኛለን። በዮሃ.4 ደግሞ አንዲት ሌላ ሴት እናያለን።
3. ያገኙትን መናገር የታማኝነት መለኪያ ነውና፤ በመመስከር እምነታችንና መንፈሳዊ ህይወታችን ያድጋል።
4. እንድንመሰክር ታዝዘናል (ማቴ.28፡19-20፣ ማር.16፡15፣ ሐዋ.1፡8) መመስከር ደግሞ የታደልንበት መጠራታችን አንድ ዓላማም ነው (1ጴጥ.2፡9-10)።

የምንመሰክረውስ ለማን ነው? እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ ይወድዳል። ስለዚህ ያልዳኑ ሁሉ ሊመሰከርላቸው ይገባል ማለት ነው። እኛ ለመመስከር በተዘጋጀንና በተመኘን መጠን እግዚአብሔርም የምንመሰክርላቸውን ሰዎች ያጋጥመናል፤እነዚህ ሰዎች ቤተሰብ፣ጓደኛና ወዳጆች፣ የስራ ባልደረቦች፣ለትንሽ ጊዜ የምንተዋወቃቸው ሰዎች ወይም በመንገድ ላይ የምናገኛቸው የማንተዋወቃቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

የምንመሰክረውስ እንዴት ነው ልንል እንችላለን? ወንጌልን በሁለት መንገዶች ነው ማስተላለፍ የምንችለው:- የመጀመሪያው የህይወታችን ምስክርነት ነው፤ በመልካም እግዚአብሔር መታየትና መክበር አለበት (ማቴ.5፡16)። አኗኗራችን፣ አመለካከታችንና ለነገሮች የምንሰጠው ግምትና ክብደት ከሌሎች ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች የተለየ መሆኑ ማንነታችንን ያሳያል (1ጴጥ.2፡12)።

ህይወታችን ድምጽ አልባ መስካሪ ነው። በህይወት መመስከር አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻውን ግን በቂ አይደለም። በአንደበታችንም የጌታን አዳኝነት መናገር አለብን። በህይወታችን የምናረጋግጠው በቃላችን የተናገርነውን ነው። ስለዚህ አንደበታችን በጎነውን ለመናገር ሁሌም የተከፈተ መሆን አለበት። ጌታ "ምስክሮቼ ናችሁ" ብሎ ለምስክርነት ጠርቶናል። መልካም ምስክሮችና አስጠንቃቂዎች ልንሆን ይገባናል (ህዝ.3፡17)።

ስንመሰክር ምን ማለት ይኖርብናል? ምስክርነታችን በአንድ ቀመር ብቻ ላይ የተመሰረተ ሊሆን አይገባውም። አቀራረባችን ሊለያይ ይችላል። ነገር ግን አቀራረቡ ቢለያይም ዋና አሳቡ ተመሳሳይ ነውና ዋናው አሳብ አራት ዋና ዋና ነጥቦች እንመልከት:-

- የእግዚአብሔር ፍቅርና ለሰው ልጆች ያለው ዓላማ
- የሰው ሁሉ ኃጢአተኛነት፣ ከእግዚአብሔር መለየትና የዚህ መለየት ዘላለማዊ ውጤት
- እግዚአብሔር የዕርቅ መንገድን በልጁ በክርስቶስ በኩል ማዘጋጀቱ
- የመታረቂያውን መንገድ ማለትም ክርስቶስን በእምነት የመቀበል አስፈላጊነት ናቸው።

ምስክርነታችንን የተቀበሉትን ወደጌታ በጸሎት ልንመራቸው ይገባናል። ያልተቀበሉት ደግሞ በነሱ አስተሳሰብ ከ እኛ አሳብ ብቻ ጋር ያልተስማሙ ይመስላቸዋል። ነገር ግን እኛን ወይም የኛን አሳብ ሳይሆን ጌታ ነው ያልተቀበሉት ልንጸልይላቸው ያስፈልጋል። ምስክርነት ደግሞ ዘርን እንደመዝራት ያለ ሂደት ነውና ፍሬው እስኪታይ ድረስ ተስፋ ባለመቁረጥ ልንጠብቅና ከዚያ በኋላም ያሉትን አጋጣሚዎች ልንዋጃቸው ይገባል።

ስንመሰክር መጠንቀቅ ያለብን ጉዳዮች፡-

- እኛ የምንመሰክር እንጂ የማንለውጥ መሆናችንን እንወቅ፤ የሚለውጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- በመንፈስ ቅዱስ መደገፍን መርሳት የለብንም።]
- የግብር ይውጣ ስራ አንስራ። *"ከኔ አይቅር እንጂ"* ብለን አንመስክር ከልብ ወደንና ጥፋታቸውም ተሰምቶን እንመስክርን።
- አንከራከር
- ብዙ በማይጠቅሙ ርዕሶች ላይ ብዙ ጊዜ አናባክን።
- አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንጠቀስ፤ የእርሱ ቃል ከኛ ንግግር ይበልጥ ኃይል እንዳለው አንርሳ።
- የማናውቀውን ጥያቄ ቢጠይቁን ከመዘባረቅ "አላውቅም" እንበል። ያለማወቅ ሰው የመሆን አንድ ባህርይ እንጂ ነውር አይደለም።
- ስንመሰክር ሰባኪ ለመሆን አንሞክር። ንግግር መደማመጥም እንዳለው አንዘንጋ
- ታማኝ እንሁን፤ እውነተኛውን እኛነታችንን ደብቀን ሸንጋይ መልክ ይዘን አንቅረብ።
- በተቻለ ወደ ውስኔ ማለትም ጌታን ወደመቀበል ወይም አለመቀበል ውሳኔ መድረስ እንቻል።

ጥያቄዎች፡-

1. መመስከር ምንድነው? ____________________

2. መመስከር ያስፈልገበት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ____________________

3. የምንመሰክረው ለማነው? እንዴትስ ነው? ____________________

4. የምስክርነታችን ዋና ዋና ነጥቦች ምን ምን ናቸው? ____________________

5. ስንመሰክር መጠቀቅ ከሚገቡን ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹን ጥቀስ። ____________________

7. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት



አንድ አማኝ ዳግም በተወለደበት ቅጽበት የእግዚአብሔር ለመሆኑ ምልክት በመንፈስ ቅዱስ ታትሟል (ዮሃ.14፡16-18፤ ሮሜ.8፡9-16፤1ቆሮ.6፡19)። በዚህም የክርስቶስ አካል ብልት ሆኗል። አንድ አማኝ ዳግም ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ሊኖርና ህይወቱን ሊመራ ጀምሯል ማለት ነው። ይህ የጅማሬ ስርዓት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይባላል (1ቆሮ.12፡3)። ከዚህም ባሻገር ደግሞ አማኝ በየቀኑ ሊኖርበትና ሊያገለግልበት እንዲችል ዳግመኛ ከተወለደ በኋላ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል። በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክቱ በልሳን መናገር ነው (ሃዋ.2፡1-6)።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተቀበለ ክርስቲያን ራሱን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ምሪትና ቁጥጥር ስር ያደርጋል ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አንድ ጊዜ የሚከሰት ሳይሆን በየእለቱ የሚሆንና መሆንም ያለበት ነገር ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚሆነው በአማኙ ተጠሚነትና ታዛዥነት ነው። ይህ በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን፣ ለአገልግሎት የምያበረታን፣ ለመታዘዝ የሚያነሳሳን መንፈስ ነው። ከክፉና ከመጥፎ ነገሮች እንዲርቅ መንፈስ ቅዱስ አማኝን ሲያስታውሰው እሺ ለማለት ምን ጊዜም ዝግጁ መሆን ይገባዋል።

መሞላት ለጥቂቶች ብቻ የተቸረ ስጦታ ሳይሆን ሁሉም አማኝ እንዲሆን የታዘዘው ትዕዛዝ ነው። ኤፌ.5፡18 “መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።” ይላል። መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ወይም የማይኖርበት ክርስቲያን የለም። በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ክርስቲያኖች ግን ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ጥቅስ መሰረት መንፈስ መሞላትና ወይን ጠጅ መጠጣት ተነጻጽሯል። ይህ ማለት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ልክ በወይን ጠጅ ስካር ውስጥ ያለ ሰው በመጠጡ ኃይል የማይደረግ እንደሚያደርግ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያደርጋል ማለት ነው። ሲሰክር ትሁት የነበረው ጉረኛ፣ ዓይን አፋር የነበረው ዓይን አውጣ፣ ፈሪ የነበረው ደፋር ይሆናል። እንዲሁ ሁሉ ክርስቲያንም በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ

የሚጠላውን መውደድ፣ በኃዘን መካከል መጽናናት፣በትርምስና ሁካታ መሃል ዕረፍትና ሰላም፣ ሌሎችም የበዙ ውብ የመንፈስ ቅዱስ ስራዎች በህይወቱ ይታያሉ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ህይወቱ ይመሰክራል፤ በፍሬ የተሞላ ነው። በገላ.5፡22-23 እንደተጻፈልን የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም፣ትዕግስት፣ቸርነት፣በጎነት፣ታማኝነት፣የዋህነት፣ራስን መግዛት ነው። እነዚህ ነገሮች በህይወታቸው የሚታዩ አማኞች በመንፈስ የተሞሉ ናቸው። ከዚህም ባሻገር መንፈስ ቅዱስ ባደላቸው በማናቸውም የጸጋ ስጦታዎች በሚያገለግሉበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ይታነጹባቸዋል፤ እግዚአብሔርም በህይወታቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው ይከብራል።

ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልዩነት ምንድናቸው? ________________

____

____

____

____

____

2. በመንፈስ መሞላት በወይን ጠጅ ከመስከር ጋር ምን መመሳሰል አለው? ________________

____

____

____

____

3. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው በምን ይታወቃል? ________________________

____

____

____

____

____

ሐ. ደቀ መዝሙር



ደቀ መዝሙር ማለት ከላይ ባለፉት ትምህርቶች በተመለከትናቸው መንፈሳዊ የዕድገት አቅጣጭ ዘርፎች እያደገ ያለ ክርስቶስ ተከታይ ማለት ነው። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ቋንቋ ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል “ማቴቴስ” የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል በጥሬው ሲተረጎም ተማሪ ማለት ቢሆንም ግን የተለየ ዓይነት ተማሪ ነው። የተለየ የሚያደርገውም የእርሱ ስራ እንደሌሎች ተማሪዎች ዕውቀትን ሰብስቦ በጭንቅላት መቋጠርና ሲጠየቁ ወይም በፈተና ጊዜ መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን የሚማረውንና የሚታዘዘውን የሚያደርግ አድራጊ ተማሪ ተከታይ መሆኑ ነው። ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራ ከፍተኛ ዋጋ እንዲከፍሉ ጠይቋቸው ነበር (ለምሳሌ ማቴ.10፡24-39፤ ሉቃ.9፡23፤ 14፡26-33)።

ደቀ መዛሙርትም ሲከተሉት ዋጋቸውን ተምነው ነበር የተከተሉት። ይሁን እንጂ የተከተሉት ሁሉ እርሱን የሚመስሉ ፍጹማን አልነበሩም። አንዳንዴ መንፈሳዊ ድንዛዜ ይይዛቸው ነበር (ማቴ.13፡36፤ 16፡6-11፤ ዮሃ.15፡5-10)። መንፈሳዊነታቸው ደክሞ እምነት የሚያጡበት ጊዜ ነበር (ማቴ.17፡15-20)። የሰይጣን መሳሪያ የሆኑበት ጊዜም እንኳ ነበር (ማቴ.16፡21-23፤ 26፡14-16)። በትዕቢት የሚኩራሩባቸውና ስልጣን ፍለጋ የተጠሙባቸውም ጊዜያትም ነበሩ (ማር.10፡35-45)። ራሳቸውን ሳይሰጡ ሲከተሉ ቆይተው ወደ ኋላ ያፈገፍጉም ነበሩ (ዮሃ.6፡66) ለሌሎች ደስታ ደንታ ያልነበራቸው ጊዜም ነበር (ማር.10፡13-14)። እንግዲህ እንዲህ አሉት ያሉት ናቸው ተከታዮች ወይም ደቀመዛሙርት ተብለው የተጠሩት።

ከዚህ እንደምንረዳው ደቀመዝሙር ማለት ተሰርቶ ያለለቀ ገና በመሰራት ሂደት ውስጥ ያለ ዕቃ የሚመስል ሰው ነው። ደቀመዝሙር ክርስቶስን ለመምሰል ራሱን ሰጥቶ ከቀን ወደ ቀን እርሱን በመምሰልና የበለጠም ራሱን በመስጠት የሚያድግ አማኝ ነው። መቼ ነው ተሰርተን የምናልቀው ቢባል በዚህ ቀን ነው ማለት አይቻልም። የመቀረጻችን ሂደት እስከ እለተ ሞታችን ድረስ የሚረዝም ነው። ተግባራዊ የሆነ ታዛዥ ክርስቲያን ከታች ያለውን ስዕል ይመስላል።

ትልቁ ክብ የክርቲያንን ህይወት የሚያመለክት ሲሆን መሃል ያለው ትንሽ ክብ ደግሞ የክርስቶስ ኅልውና አመልካች ነው። አንድን ክርስቲያን ክርስቲያን የሚያደርገው ከሌሎችም ሰዎች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው የክርስቶስ በርሱ ህይወት ውስጥ መኖር ነው ማለት ነው። ክርስትና የሚጀምረው ከክርስቶስ ጋር ከተመሰረተ ግንኙነት ነው። ክርስቶስ በውስጡ የሌለ ሰው ሰው ክርስቲያን አይደለም። ወደ አራቱም አቅጣጫዎች የተዘረጉት አራት መስመሮች አራቱን ዋና ዋና የማደጊያ መንገዶች ያመለክታሉ። እነዚህም የጸሎት፣ የቃሉ፣ የህብረትና የምስክርነት መንገድ ናቸው።



እነዚህ አራት ዋና የመንፈሳዊ ህይወት ማደጊያ መንገዶች ቀደም ብለን የተመለከትናቸው ቢሆንም ደቀ መዝሙር በእነዚህ አራት አቅጣጫዎች ማደግ የሚጠበቅበት ነገር መሆኑን መድገሙ አስፈላጊ ነገር ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከአራቱ በአንዱ አቅጣጫ ብቻ የጎላ እድገት ቢያስመሰክሩም ሌሎቹ ደግሞ መዘንጋት የሌለባቸው መሆኑ መታወቅ አለበት። ከዚህ በታች ያሉትን ክቦች ብንመለከት በተለያዩ አቅጣጫዎች ያለቅጥ መለጠጥን ያሳያሉ። ከትክክለኛው ጋር አወዳድሯቸው።



እነዚህ ክቦች እንደሚሽከረከሩ ጎማዎች ቢሆኑ የቱ ነው ያለ ምንም ችግር ኮለል እያለ የሚሄደው? የመጨረሻው መሆኑ ግልጽ ነው። የደቀ መዝሙር የእድገቱ ሚዛን የተጠበቀ መሆን ይገባዋል። እንዲህ ከሆነ ነው ሚዛናዊና አሸናፊ የሆነ የክርስትና ህይወትን መኖር የሚቻለው ማለት ነው።

ጥያቄዎች

1. በአዲስ ኪዳን ቋንቋ (ግሪክ) ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? ____________

____

____

____

2. ደቀ መዛሙርት ሲከተሉ የተጠየቁት ዋጋ ምን ነበር?______________________________

____

____

____

____

3. ደቀ መዛሙርት ፍጹማን ነበሩ? ምሳሌ ስጥ______________________________

____

____

____

4. የተግባራዊ ደቀ መዝሙር አራት የእድገት አቅጣጫዎች ምን ምን ናቸው?_______________

____

____

____

5. አራቱ አቅጣጫዎች ተዛብተው ማደግ የሌለባቸው ለምንድነው? ትክክል የሆነ እድገትስ ምን ጥቅም አለው?______________________________________

____

____

____

____

3. ቤተ ክርስቲያን

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድናት?

በተለምዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት በጥሬ ቃሉ የክርስቲያን ቤትን ወይም የጸሎት ቤትን ወይም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያን ሊያመለክት ይችላል። መንፈሳዊ አተረጓጎሙ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። ቤተ ክርስቲያን የተባለው የአዲስ ኪዳን ቃል "ኤክሌሲያ" የሚለው ሲሆን በሰፊው ትርጉሙ ማናቸውም ጉባዔ ማለት ነው (ሐዋ.7፡38፤ 19፡32፤41)።

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎሙ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ማለት የአማኞች ጉባዔ ወይም ኅብረት ማለት ነው (1ቆሮ.1፡2፤ ገላ.1፡13)። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ማለት ህንጻው ሳይሆን አማኞቹ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን በሁሉ አቅጣጫ ማክበር ነው (ኤፌ.1፡6፤12፤14)። ተግባሮቿ ደግሞ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

1. ወንጌልን ለዓለም ማዳረስንና አማኞችን ማጥመቅን ማስተማርንና ደቀ መዛሙርት ማድረግን - ማቴ.28፡19-20
2. አማኞችን መገንባትንና ማነጽ/ማሳደግን - ኤፌ.4፡11-16
3. ለአማኞች የአገልግሎት መስክ መሆንን - 1ቆሮ.12
4. አማኞች ጥፋትን ሲያጠፉ መገሰጽንና መቅጣትን - ማቴ.18፡17፤1ቆሮ.5፡1-13፤ 2ተሰ.3፡14-15
5. ለአማኞች የኅብረትን መስክ መፍጠርን - ሐዋ.2፡42
6. የራሷ የሆኑትን በችግራቸው መርዳትን - 2ቆሮ.8፡9፤ያዕ.1፡27
7. መልካም የሆነውን ሁሉ ማድረግን - ገላ.6፡10

ዳግም በተወለዱና መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በኖረ አማኞች የተሰራችው ይህች ቤተ ክርስቲያን የምትባለው አካል የተወለደችው ወይም የተመሰረተችው በበዓለ ኀምሳ ቀን ነው (ሐዋ.2፡1-4፤ 37-42)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ምዕመን አገልግሎት ያላቸው ቢሆኑም በተለይ በመምራት አገልግሎት የተሰማሩት ሹሞች ከኃላፊነታቸው ጋር ተጽፈዋል። ከእነዚህ ሁለቱ ዋና ዋናዎቹ ኤጲስ ቆጶሳትና (1ጢሞ.3፡1-7) እና ዲያቆናት (1ጢሞ.3፡8-12) ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምን መምሰል እንደሚገባቸውም ከላይ ያሉት ጥቅሶች ያወሳሉ።

ጥያቄዎች፡

1. የቤተ ክርስቲያንን ተለምዷዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም ስጥ ____________________

2. የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ ምንድን ነው? ____________________

3. ከቤተ ክርስቲያን ተግባራት መካከል ጥቂቱን ጻፍ። ____________________

4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተሰጡት ሹመቶች የጎሉት የትኞቹ ናቸው? ____________________

ለ. ቤተ ክርስቲያን የምትመሰልባቸው ምሳሌዎች

ቤተ ክርስቲያን ምንና ማን መሆንዋን የበለጠ እንድንረዳ በተለይም ከክርስቶስ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማብራራት መጽሐፍ ቅዱስ ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ይገልጣታል። እነዚህ መግለጫዎች ዋና አላማቸው የቤተ ክርስቲያንንና የክርስቶስን ግንኙነት ለማሳየት ነው። እነዚህም ግንኙነቶች የተገለጡባቸው ስድስት ዋና ዋና መግለጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. *ራስና አካል* - (ሮሜ.12፡4-5፤ 1ቆሮ.12፡12-13፤ ኤፌ.4፡4፤ ኤፌ.5፡30፤ ቆላ.1፡18) - ከዚህ አሳብ እንደምንረዳው ክርስቶስ ራስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካል ናት። እንደመሆኗም መጠን ራስ የሆነውን ክርስቶስን መታዘዝ፣በደስታ ማገልገልና መተባበር ይገባታል። አማኞች በአካል መመሰላቸው እያንዳንዱ አማኝ ብልት መሆኑን የሚያመለክት ነው። እያንዳንዱ ብልት ልዩ ልዩ ቢሆንም ማንም ከማንም አይሻልም። አንዱ ደግሞ ከሌላው መለየት የለበትም።

2. *ሙሽራና ሙሽሪት* - (2ቆሮ.11፡2፤ ኤፌ.5፡25-32፤ ራዕ.21፡9) - ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው ሙሽራው ወይም ባል የሆነው ክርስቶስ ሲሆን ሙሽሪት ወይም በሚስት የተመሰለችው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ያለ ገደብ እንዳፈቀረ እንረዳለን። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለዚህ ፍቅር ምላሽ ለመስጠት ንጹህ መሆንና መታዘዝ እንደሚገባት መረዳት እንችላለን።

3. *ግንድና ቅርንጫፍ* - (ዮሐ.15፡1-5) - ከዚህ ግሩም ምንባብ እንደምንረዳው ክርስቶስ ተሸካሚው ግንድ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ወይም አማኞች ደግሞ ቅርንጫፍ ናቸው። ቅርንጫፍ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይጠበቅበታል፦
   - በግንዱ መኖር
   - ፍሬ ማፍራት፣ ብዙ ፍሬ ማፍራት፣ የግንዱን

ባህርይ የያዘ ፍሬ ማፍራት (ኢሳ.5፡1-7)፣ የወይን ቅርንጫፍ ከፍሬ በቀር ሌላ ምንም ጥቅም አይሰጥም፤ቤት አይሰራበትም፤ የቤትም እቃዎች አይታነጹበትም (ህዝ.15፡2)።

- ለመገረዝና ለመጥራት እሺ ማለትና መስማማት

4. *እረኛና መንጋ* - (ዮሃ.10፡11፤ዕብ.13፡20፤1ጴጥ.5፡20፤መዝ.23) - ክርስቶስ ለነፍሱ ሳይሳሳ ሞት ያዳናት የቤተ ክርስቲያን እረኛ ነው። ቤተ ክርስቲያንም የእረኛዋን ድምጽ መስማትና እርሱን መከተል ይጠበቅባታል።

5. *ሊቀ ካህናትና የካህናት መንግስት* - (1ጴጥ.2፡9፤ራዕ.1፡6፤5፡10፤20፡6) - አማኞች እንደ ካህንነታቸው ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ለሌሎቹ የመማለድና መስዋዕት የማቅረብ ዕድል አላቸው። መስዋዕቶቹም የሚከተሉት ናቸው፦
   - ሰውነታቸው - ሮሜ.12፡1
   - ገንዘባቸው - ለሌሎች ማካፈላቸው - ፍል.4፡18፤ዕብ.13፡16
   - ምስጋናቸው - 1ጴጥ.2፡5፤ዕብ.13፡15
   - መልካም ስራቸው - ዕብ.13፡16



6. *የማዕዘን ራስ ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች* - (ኤፌ.2፡19-22፤1ቆሮ.3፡10-11፤1ጴጥ.2፡4-5) - ክርስቶስ የህንጻው መሠረትና የማዕዘኑ ድንጋይ ነው፤ሕንጻው ደግሞ የተሰራው በአማኞች ሁሉ ነው። እያንዳንዱ አማኝ እንደ ድንጋይ ይመሰላል። እያንዳንዱ ድንጋ ደግሞ ለህንጻው አስፈላጊ እንደመሆኑ እያንዳንዱም አማኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር በሌላ በማንምማ በምንም ላይ መመስረት አይገባትም። የማዕዘን ራስ ማለት የህንጻ የርዝመት፣የወርድና የከፍታ አቅጣጫዎች የሚመሰረቱበት ዋና ድንጋይ ማለት ነው።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የምትመሰልባቸው እነዚህ ምሳሌዎች የአማኝንና የምዕመንን ግንኙነት የሚያመለክቱ አመልካቾች ጭምር ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ምሳሌዎች የክርስቶስን ማንነትና የአማኝን መብትና ኃላፊነቶችም ያሳያሉ።

ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች የተጠቀሱበት ዓላማ ምንድነው?____________________
____
____
____

2. የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ግንኙነቶች የተመሰሉበት ስድስት ምሳሌዎች እነማን ናቸው?

ሀ.____________________ መ.____________________

ለ.____________________ ሠ.____________________

ሐ.____________________ ረ.____________________

3. የራስና አካል ግንኙነት ምንን ያመለክታል?____________________________
____
____
____
____
____

4. ቤተ ክርስቲያን በሙሽሪት በመመሰሏ ምን ትረዳለህ?______________________
____
____
____
____

5. ቅርንጫፍ የሚጠበቅበት ኃላፊነቶች ምን ምን ናቸው?

6. አማኞች እንደ ካህን ማቅረብ የሚጠበቅባቸው መስዋዕቶች ምን ምን ናቸው?

7. መሠረትና የማዕዘን ድንጋይ ለህንጻ ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆኑና ይህ ደግሞ ለክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ጻፍ።

8. አንተስ የቤተ ክርስቲያን ክፍል ነህ? በመሆንህስ ምን ይሰማሃል?

ሐ. ሁሉ አቀፍና አጥቢያ ቤት ክርስቲያን



ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ስብስብ እንደሆነች ተመልክተናል። ይህች የአማኞች ስብስብ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሁለት አይነት መልክ አላት፤ እነዚህ ሁለት መልኮች ሁሉ አቀፍ ቤተ ክርስቲያንን ማለት ክርስቶስን አምነው የተቀበሉት ከዚህ በፊት ኖረው የሞቱት፤ አሁን በህይወት ያሉትና ወደፊትም የሚኖሩት አማኞች በሙሉ የሚጠቃለሉበት ስብስብ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከተወለደችበት ከጴንጤቆስጤ ዕለት አንስቶ እስከ መጨረሻው አማኝ ድረስ ያሉት በሙሉ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጠቀለላሉ። ሁሉ አቃፏ ቤተ ክርቲያን ሁሉን ዳግም የተወለዱ አማኞች ታቅፋለች (1ቆሮ.15፡9፤ገላ.1፡13፤ኤፌ.5፡25-32)።

አጥቢያ ቤተ ክርቲያን በአንድ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚገኙ ክርስቲያኖች አንድ እምነት ስላላቸው በአንድነት ጌታን ለማምለክ፣ ቃሉን ለመማር፣ እርስ በርስም ለመተናነጽ ወንጌልን ለማዳረስና የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ሁሉ ለመፈጸም በአካባቢያቸው የተደራጁ ምዕመናን ስብስብ ናት።

አጥቢያ ማለት አካባቢ፣ቀበሌ፣ክልል እንደማለት ነው። እነዚህ ምዕመናን በህንጻ ውስጥ አመለኩ ወይም በቤት አጥቢያ፤ አጥቢያ ተብለው ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ፦ ኢየሩሳሌም፣ፍልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ ኤፌሶን፣ በሮም በአቂላና ጵርስቅላ ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምስሌዎች ናቸው።

ዛሬም በዘመናችንና በአካባቢያችን የሚገኙ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልንጠራ እንችላለን። የጽዮን ክብር ቤተ ክርስቲያን በቫንኩቨር ቤተ ክርስቲያን፤ የመሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን፣ የተቀባ የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያን፣ በሞንትሪያን የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣በለንደን ኦንታሪዮ የእምነተ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንና በሲያትል የሮሆቦት ቤተ ክርስቲያን ወዘተ. እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።

አንድ ህጻን ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ከቤተሰቡ እንደሚደባለቅ አንድ አማኝ ዳግም ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ከሁሉ አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተደባልቋል። ከዚህ በኋላም ቶሎ ብሎ በአጥቢያው የምትገኝ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁሉ አቀፏ ቤተ ክርስቲያን በአካላዊ መልክ የምትገለጠው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማዳረስ የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችን ማለትም የጌታን ራትና የውኃ ጥምቀትን ለመፈጸም፣ ህብረት ለማድረግና እርስ በርስ ለመተናነጽ ዓይነተኛዋና ብቸኛዋ መስክ ናት። አንድ ሰው ድነትን ሲቀበል ፍጹም ሆነ ማለት ስላይደለ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ፍጹማን አይደሉም። እንዲያውም ምናልባት የዳኑ የሚመስሉ ግን ያልዳኑ ሰዎች ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት በስህተት ሊገቡ ይችሉ ይሆናል።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችና አገልጋዮች አሉ። እነዚህ ሁሉ የሚገለጡትና ገንቢነታቸው በተግባር የሚታየው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። በመጀመሪያ ጌታ የሾማቸው ሐዋርያትን ነበር። ሐዋርያ ማለት የተላከ ወይም መልዕክተኛ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ሃዋርያት ጌታ ራሱ የሾማቸው ከርሱ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ። ቀጥሎ ዲያቆናት የቤተ ክርስቲያን ማህበራዊ መሪዎች (የሃዋርያት ረዳት) ሆነው ሲያገለግሉ እናነብባለን።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ መሪዎች በተለያዩ መጠሪያዎች ተጠቅሰዋል፡-

- ኤጲስቆጶስ - 1ጢሞ.3፡1-2፤ ቲቶ.1፡7
- ጳጳስ - ሐዋ.20፡28
- መጋቢ - ቲቶ.1፡7
- እረኛ - 1ጴጥ.5፡1-4

እነዚህ ሰዎች ኃላፊነታቸው ምዕመናንን መጠበቅ፣መልካም ምሳሌ መሆን፣ማስተማር፣መምከር፣መገሰጽ፣መጎብኘት ወዘተ ... ነው። ከመሪዎች አገልግሎት ጋር በመተባበር ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ዲያቆናት የሚባሉ አገልጋዮች ደግሞ አሉ (ሐዋ.6፡1-6)። የዲያቆናት ተግባር የመሪዎችን አገልግሎት መርዳት ወይንም ማገዝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት፣ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣መጋቢዎችና አስተማሪዎች ተደርገው የተሰጡ ሰዎች አሉ (ኤፌ.4፡11)።

ከዚህም ሁሉ ባሻገር ምዕመናን ሁሉ የጸጋ ስጦታ የተሰጣቸው የአካሉ ብልቶች እንደመሆናቸው መጠን እያንዳንዳቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታን ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ መታነጽ ስለሰጠም እያንዳንዱ ም ዕመን በተሰጠው ስጦታ ጉባዔውን እንዲያንጽ ይጠበቅበታል።

ሁሉም ም ዕመን በተጨማሪ የተቀደሰ ኑሮን በመኖር፣ወንጌልን ላልሰሙ በማሰማት፣እርስ በርስ በመተናነጽና በመገነባባት፣በታማኝነት በማምለክና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በመሳተፍ፣ በውዴታና በደስታ ለወንጌል አገልግሎት የሚውል የገንዘብ ስጦታን በመስጠት እግዚአብሔርን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ሁለት የመገለጫ መልኮች ምን ምን ናቸው?____________________

2. ሁሉ አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?____________________

3. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንስ? ____________________

4. አንድ አማኝ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆን ለምን ያስፈልገዋል? ____________________

5. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪ አገልጋዮች የትኞቹ ናቸው? ____________________

6. መሪዎች የተጠሩባቸው የተለያዩ ስሞች እነማን ናቸው? ____________________

7. እያንዳንዱ ምዕመን አገልጋይ ነው ወይስ አይደለም? ____________________

መ. የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ስርዓቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ ሁለት ስርዓቶች የውሃ ጥምቀትና የጌታ ራት የሚባሉት ስርዓቶች ናቸው። ስርዓቶቹ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስለሆነ ምዕመናን ደግሞ በስርዓቱ ተሳታፊ መሆን ይገባቸዋል።

1. የውሃ ጥምቀት

በብሉይ ኪዳን ህግ ሰው ወይም ዕቃ ቢረክስ በውሃ በመረጨት ወይም በመታጠብ ይነጻ ነበር (ዘኊ.19፡1-10፤ ዕብ.9፡9-10) የአዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት ከብሉይ ኪዳን ህግ የተለየ ነው። የአዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት ለመንጻት ሳይሆን ለመመሳሰል (ለመዋሃድ) የሚደረግ ስርዓት ነው።

በአዲስ ኪዳን የውኀ ጥምቀት ወይም ማጥመቅ የሚለው ቃል የተወሰደበት የግሪክ ቃል (baptizo) ባፕቲዞ የሚለው ሲሆን ትርጓሜው መድፈቅ፣ ውሃ ውስጥ መቅበር፣ ሙሉ በሙሉ ማጥለቅ ወይንም ማስጠም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱአዊው የውኀ ጥምቀት ትርጉም መመሳሰል ማለት ነው። የውኀ ጥምቀት ጌታ ያዘዘው ትዕዛዝ ነው (ማቴ.16፡30-31)።

መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው? ብለን ብንጠይቅ እንደመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ያመኑ ሁሉና ያመኑ ብቻ መጠመቅ አለባቸው (ሐዋ.2፡41፤ 8፡12፤ 36-38፤ 16፡14-15፤ 30-33፤ 18፡8፤ 19፡4-5)። የውኀ ጥምቀት ምሳሌያዊ የውህደት ወይም የአንድነት መግለጫ ድርጊት ነው፤ የሚያመለክተውም አማኝ ከክርስቶስ ጋር መመሳሰሉን ነው (ሮሜ.6፡1-10፤ ቆላ.2፡11-13)። አንድ አማኝ ክርስቶስ ባመነ ጊዜ የተለወጠውን የውስጥ ለውጥ በውጪያዊና በሚታይ መንገድ በአደባባይ በውኀ ጥምቀት ይመሰክራል።

የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ከክርስቲያን ጥምቀት የቀደመ የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ነው። የዮሐንስ ጥምቀት ዋና ዓላማ ስለመሲህ ማለት ስለክርስቶስ በመስበክ ሰዎች ንስሃ ገብተው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁትና ሲመጣም

እንዲቀበሉት ለማድረግ ነበር (ማቴ.3፡11-12፤ማር.1፡1-8፤ ሉቃ.3፡3-6)። ጌታማ ራሱ በ30 አመቱ በማየ ዮርዳኖስ (በዮርዳኖ ውኀ) በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። ጌታችን የተጠመቀው ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ኃጢአቱን ለመናዘዝ ወይም ለመዘጋጀት ሳይሆን ጽድቅ ሁሉ ለመፈጸምና መሲሁ እርሱ መሆኑን ለመግለጥ ነበር (ዮሐ.1፡29-34)

ክርስቲያን በውኀ የሚጠመቀው ለደኅንነት አይለም። አንድ ክርስቲያን የሚድነው በ እምነት ጌታን በሚቀበልበት ጊዜ እንጂ ጥምቀትን ጨምሮ በሌላ በማናቸውም ስራ አይደለም። አንድ ክርስቲያን የሚምጠመቅበት ምክንያት የጌታ ት ዕዛዝ ስለሆነ እርሱን ለመታዘዝ እና የውስጡን ለውጥ በውጪያዊ መግለጫ ለመግለጥ ማለትም ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ መነሳቱ ለማወጅ በዚህም ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ መሆኑን ለማሳወቅ ነው።

ማንም ክርስቲያን የወንጌሉን የምስራች ቃል ከሰማ በኋላ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን እንደ ግል መድኃኒቱ ከተቀበለ በኋላ የውስጡን ለውጥ በጥምቀት መመስከር እንደሚገባው ካወቀ መጠመቅ ይችላል። አንድ ክርስቲያን መጠመቅ ያለበት እንደ ጌታ ትዕዛዝ በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በኢየሱስ ስም የመጠመቅ ነገር ተዘግቧል። ይህ ማለት የመጀመሪያው አሳብ መሻሩ ሳይሆን በወቅቱ ኢየሱስን እንደ መሲህ ለመቀበል የነበረውን ችግር ለማስወገድ አትኩረትን በኢየሱስ ላይ ለማድረግ ነው እንጂ ትምህርተ ሥላሴን ውድቅ የማድረጋቸው እርምጃ ወይም “በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም” የተባሉትን መሻራቸው ወይም በዚያ ስም ያለማጥመቃቸው አልነበረም። ሰው አንድ ጊዜ ካመነ በኋላ መጠመቅ አለበት።

ጥያቄዎች

1. በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት ሁለት ስርዓቶች ምንና ምን ናቸው? ____________

2. የብሉይ ኪዳን የመርጨት ስርዓት ዓላማ ምን ነበር? ____________

3. የአዲስ ኪዳን ማጥመቅ የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊውስ? ____________

4. መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው? ____________

5. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ዓላማ ምን ነበር? ጌታስ ለምን በእርሱ ተጠመቀ? ____________

6. አንድ ክርስቲያን የሚጠመቀው ለምንድነው? ________________________________

7. ክርስቲያን መጠመቅ ያለበት መቼ ነው? ________________________________

8. አንተስ ጌታን ከተቀበልክ በኋላ ተጠመቀሃል? ለመጠመቅስ ታስባለህ? የምታስብ ከሆነ የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች ማነጋገር ይኖርብሃል። ________________________________

2. የጌታ ራት

ሌላው በቤተ ክርስቲያን የተሰጣት መጠበቅ ያለባት ስርዓት የጌታ ራት መታሰቢያ ወይም ቅዱስ ቁርባን የሚባለው ነው (ማቴ.26፡26-30፤ ማር.14፡22-26፤ ሉቃ.22፡17-20፤ 1ቆሮ.11፡23-34)። “ቁርባን” የሚለው የግዕዝ ቃል “መቅረብ” ከሚለው የዕብራይስጥ ስርወ-ቃል የወጣ ነው። በብሉይ ኪዳን በዘጸ.12 የዚህ ስርዓት ስር የሆነውን የፋሲካ በግ ታሪክ እናገኛለን። ጳውሎስ በ1ቆሮ.5፡7-8 ይህን ሲያወሳና ከዚህ ስርዓት ጋር ሲያያይዘው እናያለን። ይህን ስርዓት የደነገገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። የሰጠውም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት በሚበሉበት ጊዜ ነው። የፋሲካ በዓል ዋና ዓላማ እስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው።

የጌታ ራት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሲል ስጋውን መቁረሱንና ደሙን ማፍሰሱን ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስታውሱ የሰጣቸው ስርዓት ነው። በኢየሩሳሌም በነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ስርዓት በኅብረት ያደርጉ ነበር (ሐዋ.2፡42)። ከጌታ ጋር ራቱን ሲበሉ ጌታ እንደተናገራቸው እንጀራው የስጋው፤ ጽዋው ደግሞ የደሙ ምሳሌዎች ናቸው።

እነዚህ ነገሮች መታሰቢያ ብቻ ናቸውና የሚሰሩት ከህብስትና ከወይን ነው። የጌታ ራት ወይም ቅዱስ ቁርባን በሚወሰድበት መታሰብ የሚገባቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ጌታ ስለሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ መሞቱን (1ቆሮ.11፡26) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደፊት ሊሆን ያለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽ ዓትን ነው (1ቆሮ.11፡2)።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ስር ዓት የሚሳተፉት ሊመለከቱ የሚገባቸው ሌላ አቅጣጫም አለ፤ ይህም ወደ ራሳቸው (ወደ ውስጥ ህይወት) ነው (1ቆሮ.11፡28)። ይህም ማለት የጌታ ራት መታሰቢያ ከመካፈላቸው በፊት አማኞች ራሳቸውን መመርመር ማለትም ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ መሆኑን መመርመር ይገባቸዋል ማለት ነው። በሕይወታቸው ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ቢኖር መታሰቢያውን ከመውሰድ መቆጠብና ችግሮቻቸውን ቃሉ በሚለው

መንገድ መፍታት ይኖርባቸዋል። የጌታ ራት የኃጢአት ስርየት ማግኛ ወይም የደህንነት መንገድ አይደለም። ነገር ግን በጌታ ሞት ምክንያት መዳናችንን የምናስታውስበት፣ የጌታን መምጣት ተስፋ የምናስብበትና የምንናገርበት፤ አንድ እንጀራ በመቁረሳችንና አንድ ጽዋ በመጠጣታችን በአንድነታችን የምንደሰትበት ጊዜ ነው።

አማኞች ሁሉ የጌታን ራት የመካፈል መብት አላቸው። የሚካፈሉት ሁሉ ግን የተገባቸውና የገባቸው ሊሆኑ ያስፈልጋል (1ቆሮ.11፡27-32)። የተገባቸው ማለት ከላይ እንደተመለከትነው የዳኑና (ደህንነትን ያገኙ) በተጨማሪም በዚያ ጊዜ ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ የሆነ ማለት ነው። የገባቸው ማለት ደግሞ የጌታ ራት ምንነቱን የተረዱ ማለት ነው። ያለአግባብ የጌታን ራት መካፈል ድካምን፣ ህመምን፣ ስጋዊ ሞትን ፍርድንና ኩነኔንም ያስከትላል።

ክርስቲያኖች የጌታን ራት በሚካፈሉበት ጊዜ ብቃታቸው በጸጋው ብቻ መሆኑን በመገመትና በትህትና፤ ራስን በመመርመርና በመናዘዝ፤ የጌታን ሞትና የሰጠንን ደኅንነት በማሰብና በባለውለታነት፤ ዳግመኛ እንደሚመጣ በማሰብና በባለተስፋነት ከሞቱም የተነሳ ከሌሎች ጋር ስላለን ኅብረት በመደሰት፤ ለሌሎችም ሞቱን ለመናገር በመዘጋጀት መሆን ይገባዋል።

ጥያቄዎች

1. የጌታ ራት ስርዓት የተጀመረው መቼ ነው? ____________________

2. የጌታ ራት ስርዓት መታሰቢያ ብቻ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ____________________

3. የጌታ ራት ሲወሰድ መታሰብ የሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን ናቸው? ____________________

4. የስርዓቱ ተሳታፊዎች የገባቸውና የተገባቸው መሆን አለባቸው ሲባል ምንድነው? ____________________

5. ያለ አግባብ በቅዱስ ቁርባን መሳተፍ ምን ጉዳት አለው? ____________________

6. ክርስቲያኖች ይህን ስርዓት ለመፈጸም ማድረግ ያለባቸው ዝግጅት ምንድነው? ____________________

4. አገልግሎት

ሀ. የአገልግሎት ምንነት

አገልግሎት ማለት እያንዳንዱ ክርስቲያን በተሰጠው የጸጋ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሰማራበት ጊዜ የሚያበረክተው ድርሻ ማለት ነው። ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ስለቤተ ክርስቲያን ስንማር ቤተ ክርስቲያን እንደ አካል ስትታይ እያንዳንዱ ም ዕመን ደግሞ ብልት መሆኑን ተመልክተን ነበር (1ቆሮ.12)።

እያንዳንዱ ብልት አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን አንዱም ብልት ከሌላው የማይበልጥና የማይሻል መሆኑ ግልጽ ነው።

ሮሜ.12፡1-8 ሰውነታችን ለጌታ የተሰጠና ለአገልግሎቱም የሚውል መስዋዕት መሆን እንዳለበት፤ ይህም ሰውነት ደግሞ አካል ማለትም እንደ ቤተ ክርስቲያን ብልትነት በስጦታው መሰማራት እንደሚገባው ያስተምረናል። በተለይም ከቁጥር 6-8 ስጦታዎችን ይዘረዝራል። ሌሎችም ስጦታዎች የተዘረዘሩባቸው ቦታዎች አሉ። ለምሳሌ 1ቆሮ.12፡8-10፤ 28-31፤ 13፡1-3፤ ኤፌ.4፡11፤ 1ጴጥ.4፡9-11 ሌሎችም። በእነዚህ ጥቅሶች ከተዘረዘሩት መካከል ማስተማር፣ መምከር፣ መስጠት፣ ማስተዳደር፣ መፈወስ፣ ተአምራትን ማድረግ፣ ትንቢት መናገር፣ በልዩ ልሳን መናገርና ማስተናገድ ወዘተ. ይገኙባቸዋል።

እነዚህ ስጦታዎች የጸጋ ስጦታዎች የሚባሉበት ምክንያት በልምምድ ወይም በትምህርት ወይም በተፈጥሮ ችሎታ የሚገኙ ሳይሆኑ ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለአማኞች የሚሰጣቸው ስጦታዎች ስለሆኑ ነው። የጸጋ ስጦታ የሌለው አማኝ የለም። እያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ስጦታዎች አሉት። ስጦታዎቹን ማወቅና በዚያም ለማገልገል መሰማራት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነትና አደራ ነው።

በማቴ.25፡14-30 ጌታቸው መክሊት የሰጣቸውን ባሮች ታሪክ እናገኛለን። ለሁሉም እኩል አልተሰጠም። ነገር ግን እንደ ዓቅማቸው ነበር የተሰጣቸው። በተሰጣቸው መክሊት ትክክል የሰሩ ነበሩ፤ ያልሰሩበትም ነበሩ። ያተረፉት ሲሸለሙ ያልሰሩበት ደግሞ ተወሰደባቸው፤ አልፎም ቅጣትን ተቀበሉ። ይህ ምሳሌ የሚያስተምረን ሁሉም አማኝ መክሊት ወይም ስጦታ እንደተሰጠውና በስጦታው ደግሞ ሊሰራበትና ሊያተርፍ እንደሚጠበቅበት ነው።

ጥያቄዎች

1. አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?

2. የጸጋ ስጦታ ማለትስ? ከስጦታዎቹ ጥቂቶቹን ዘርዝር

3. ስጦታ የተሰጣቸው ወይም ማገልገል የሚችሉት ክርስቲያኖች ምን ያህሎቹ ናቸው?

4. አንተስ የጸጋ ስጦታ እንዳለህ ታምናለህን? ያለህ ስጦታ ምን ይመስልሃል?

ለ. በአገልግሎት ማደግ

ካለፈው ትምህት እንደምንረዳው እያንዳንዱ ክርስቲያን ስጦታ የተሰጠውና ማገልገል የሚጠበቅበት ነው። የጸጋ ስጦታ የሌለው ክርስቲያን የለም። ስጦታዎች የተሰጡት ለራስ መገንቢያ ሳይሆን ለአካል ጥቅም ነው። እያንዳንዱ ምዕመን አካሉን የመገንባትና የማነጽ ኃላፊነት አለው ማለት ነው። ዝም ብሎ የተቀመጠ ቢላዋ እንደሚደንዝ ወይንም በልቶ የማይንቀሳቀስ ሰው ቅርጹ እንደሚበላሽ የማያገለግል ጉልት ክርስቲያንም አስቸጋሪ ሰው ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያን እንደ እስታዲየም ብዙ ተመልካቾች ጥቂት ተጫዋቾችን የሚያዩበትና ሆ! እያሉ የሚጮኹበት ሜዳ ሳትሆን ሁሉም የሚሳተፍበት እርሻ ወይም ማሳ ናት። ሙሴ ፈርዖንን ያለው በዘጸ.8፡1 “ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ” ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡ ሁሉ እንዲያገለግሉት ይወዳል። በ1ጴጥ.2፡9 የእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ ካህናት መሆናቸው ተጽፏል። ሁሉም አገልጋዮች ናቸው ማለት ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙ የአገልግሎት በሮች ስላሉ እነዚህን ማወቅና በዚያም መሰማራት ለአንድ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ አገልግሎት ወይም አገልጋይ ሲባል የሚታሰበው መስበክ፣ማስተማር፣አምልኮ መሪነት፣ መዘመር፣ ማስተናገድ ወይም በአጠቃላይ በመድረክ ላይ የሚታዩትን አልያም ሙሉ ጊዜ የሚጠይቁት አገልግሎቶች ይመስሉናል። እውነቱ ግን ይህ አይደለም። ለምሳሌ መምከር የአንድ ለአንድ አገልግሎት ነው፤ መለገስ የሚታይ ወይም እዩልኝ የሚባል አገልግሎት አይደለም። ስለዚህ አንድ አማኝ የተሰጠውን ስጦታና መሰማራት የሚገባውን ስፍራ መረዳት ብሎም ከቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች ጋር በመነጋገርና በመጸለይ ሊያሰማራ በሚችልበት መስክ መሰማራት ኃላፊነቱ ነው።

ማገልገል በረከት አለው። በማገልገል ውስጥ ማደግ አለ። ከሌሎች አማኞችና ክርስቲያኖች ጋር መቀራረብና አብሮም መታነጽ አለ። አንዳንዶች አገልግሎቶች የቡድን አገልግሎቶች

እንደመሆናቸው መጠን ኃላፊነትን መካፈል አንድ በረከት ነው። በማገልገል ውስጥ ሌላው ሲታነጽ ማየትም ሌላው የበረከት ምንጭ ነው። እያንዳንዱ ምዕመን መሳተፍ የሚገባው የጋራ የአገልግሎት መስኮች መኖራቸውም መረሳት የለበትም። ለምሳሌ መጸለይ፤ መመስከር፤ አስራትንና መባን በመስጠት በገንዘብ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት መደገፍና የመሳሰሉት ለጥቂቶች ብቻ የተሰጡ ስጦታዎች አለመሆናቸው መታወቅ አለበት። በእርግጥ ከሌሎቹ የበለጠ ወንጌልን የመመስከር ወይም የመለገስ ስጦታ ያላቸው ቢኖሩም ቅሉ ሁሉም ደግሞ የሚካፈሉበት መሆኑም ግልጽ ነው።

ጥያቄዎች

1. እያንዳንዱ ምዕመን ማገልገል የሚገባው ለምንድነው? ______________________________

____

____

____

____

2. ማገልገል ለአገልጋዩ ምን ጥቅም አለው? ______________________________

____

____

____

____

3. አማኞች በሙሉ የተሰጣቸው አገልግሎቶች አሉ? ለምሳሌ ምን? ____________________

____

____

____

____